# ድሬ

19ኛ ዓመት | ቁጥር 851 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ | ጥቅምት / 28 / 2016 ዓ.ም





# የድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጠና ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት እየተሰራ ነው





በበድሉ ሀይሌ

የነፃ ንግድ ቀጠና ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ ሚና እንዲያበረክት እየተሰራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ ተናገሩ፡፡ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠናን በሙሉ አቅም ወደ ስራ ለማስገባትና ለቀጠናው በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ የሚመክር አገር አቀፍ ውይይት ባሳለፍነው ሳምንት በአስተዳደራችን ተካሂዷል።

በውይይቱ መክፈቻ ላይ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ፤ አምና በከፊል ስራ የጀመረው የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና የተሻለ ስራ መስራቱን ገልፀዋል። እስከ አሁን በነፃ የንግድ ቀጠናው ስራ ከጀመሩት በተጨማሪ ከ6 ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት ያስመዘገቡ ባለሃብቶች ከኮርፖሬሽኑ ጋር የስራ መግባቢያ ውል ተፈራርመዋል ብለዋል።

የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ረቂቅ አዋጅ ባለፈው ሳምንት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መመራቱን የጠቀሱት ኃላፊው አዋጁ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውም አንስተዋል። ረቂቅ አዋጁ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ ሲገባ ለሀገራችንና ለአካባቢው ሁለንተናዊ ዕድገት መሰረታዊ ሚና እንዲጫወት ይረዳዋል ነው ያሉት።

የድሬዳዋ አስተዳደር ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሃር በበኩላቸው ነፃ የንግድ ቀጠናው ከጅቡቲ ወደብ በቅርብ ርቀት የሚገኝ እና በሁሉም መሠረታዊ ልማቶች ከወደቡ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# በፋይናንስ አገልግሎትና አስተዳደር ስርዓት የላቀ አፈፃፀም ያላቸው የአስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት ተሸለሙ



በድሬዳዋ አስተዳደር በሚገኙ የመንግስት ተቋማት መካከል የመንግስት ፋይናንስ አገልግሎትና የፋይናንስ አስተዳደር አፈፃፀም ምዘና በማከናወን የላቀ ውጤት ላመጡ የማበረታቻ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በመድረኩም በመገኘት ሽልማቶችን ያበረከቱት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ሙሉካ መሀመድ በንግግራቸው፤ ይህ ምዘና እና ውድድር በተቋማት መካከል የአፈፃፀም ፉክክርና ውድድር በመፍጠር እንደ አስተዳደር የመንግስት ፋይናንስ አገልግሎትና የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ላይ እንዲሁም ለተቋማት የተመደበ በጀት በአግባቡ ለታቀደለት ተግባር ብቻ በማዋል የላቀ አፈፃፀም ለማስገኘት ሚናው የጎላ በመሆኑ በቀጣይ ይህን

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የራሳቸውን በጀት ለማመንጨት የሚያስችላቸውን አዲስ አሰራር ይፋ አደረጉ





በበድሉ ሀይሌ

በድሬደዋ አስተዳደር የሚገኙት ሁለቱ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ብቁ ባለሙያዎች ከማፍራት ጎን ለጎን ባላቸው እውቀትና ማሽኖች ምርቶችን በማምረት ከመንግሥት በጀት ጥገኝነት ለመላቀቅ የጀመሩት ጥረት ውጤታማ እንዲሆን የአስተዳደሩ እና የባለድርሻ አካላት ድጋፍና ርብርብ ወሳኝ መሆኑን የስራ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሮቤል ጌታቸው ተናገሩ፡፡

በድሬዳዋ የሚገኙት ሁለት የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ባሳለፍነው ሳምንት “ እያሰለጠኑ ማምረት፤ እያመረቱ ማሰልጠን “የሚል መርሃ ግብር መጀመሩን ይፋ አድርገዋል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ዝክረ ክቡር ዶ/ር አርቲስት አሊ ቢራ




በሔለን ሽጉጤ

የምስራቁ ዋርካ፣ሙዚቃን ከነሙሉ ክብሯ ለትውልድ ያሻገረው የታላቁ ከያኒ ክቡር ዶ/ር አርቲስት አሊ ቢራ 1ኛ ዓመት መታሰቢያ በተለያዩ ኹነቶች ታስቦ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

ከዕለተ ሰኞ ጀምሮ እየተካሄደ የሚገኘውመታሰቢያ ላይ በመጀመሪያ ቀን የቢልቦርድ ምርቃት ከአሊ ቢራ ፓርክ ዝቅ ብሎ ኤርፖርት መንገድ ላይ በክቡር ከንቲባውና በተጋባዥ ዕንግዶች ተመርቋል፡፡ ዝክረ አሊ ቢራ የጧፍ ማብራት መርሃ ግብርም በአሊ ቢራ ፓርክ ከምሽቱ 12፡00 ጀምሮ በማካሄድ የመታሰቢያ መርሃ ግብሩ ጅማሮውን አድርጓል፡፡

እስከ ጥቅምት 30 በሚቆየው በዚህ ኹነት የእግር ጉዞ፣ የእግር ኳስ ውድድር፣ የአሊ ቢራ ፋውንዴሽን ትምህርት ቤት፣ በክቡር ዶ/ር አርቲስት አሊ ቢራ የህይወት ታሪክ ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት፣ በድሬዳዋ የተገነቡና እየተገነቡ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች ጉብኝት፣ በክቡር ዶ/ር አርቲስት አሊ ቢራ ስም ነድያንን የማብላትና የፀሎት መርሃ ግብር፣ ሁለተኛ ቀን የኮንሰርት መርሃ ግብርና ሌሎች መርሀ ግብሮች በመታሰቢያው ላይ የሚካሄዱ ኹነቶች ናቸው፡፡

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# "ምሁር የማስጠንቀቂያ ደወል ነው ! "

አንድ ንጉሥ ወደ አደንም ሲሄድ፣ ወደ አደባባይም ሲወጣ፣ ወደ ዙፋን ችሎትም ብቅ ሲል፣ ወደ ጦር ሜዳም ሲጓዝ እንደ ቀኝ እጁ የሚያየውናእንደ ሰው አክብሮ የሚያኖረው አንድ ፈረስ ነበረው። ይህ ፈረስ በንግሥና ዘመኑ ያልተለየውና ፍፁም ባለውለታው ነበር። ስለዚህም ምን ላድርግለት ብሎ ሌት-ተቀን ሲያስብ ቆይቶ በመጨረሻ አንደ ሀሳብ አገኘ። ይህ ፈረስ ቋንቋ ቢማር እንደልብ ሊያጫውተውና ሊያናግረው እንደሚችል ታየው። ንጉሡ የሚጠላው ግን በአዋቂነቱ ምንም ዓይነት ወጥመድ ያለበት ጥያቄ ቢጠይቀው መልስ የማያጣ በመሆኑ የሚያናድደውን ሊቅ አዋቂ ምሁር አስጠርቶ እንዲህ አለው፡-

"እንደምታውቀው ይሄ ፈረሴ ባለውለታዬ ነው። በመጣምርና በመረሸት አስጊጬ፣ ገላውን በየእለቱ አሳጥቤ፣ ተገቢ የመኖሪያ ስፍራ ሰጥቼ፣ መኖሪያው እንዳይጓደል ተጠንቅቄ፣ እንደሰው አቅርቤና አክብሬ ይዤዋለሁ። ሆኖም እሱ የእኔን ንግግር ባለማወቁ፣ ቋንቋ ለቋንቋ ልንግባባ አልቻልንም። እኔ የእሱን ቋንቋ ልማር እንዳልል አንተም አስተማሪያዬ ራስህ ቋንቋውን ስለማታውቅ ማን ያስተምረኛል? ስለዚህ የሚሻለው አንተ ለፈረሴ ቋንቋ ብታስተምረው ነው። የፈለግኸውን እርዳታና የተመቻቸ ሁኔታ እንዲኖርህአደርግልሃለሁ። ታዲያ ይህ ኃላፊነት የዋዛ ኃላፊነት እንዳይመስልህ። በመሆኑም ከአሁን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ይህ ፈረስ ቋንቋ እንዲማር አድርግ። ያ ሳይሆን ቢቀር ግን ትገደላለህ!" አለው።

ምሁሩም፡-

"ንጉሥ ሆይ እርስዎ የፈለጉት እንዲሆን ማድረግና እርስዎን ማስደሰት ተገቢ መሆኑን አምናለሁ። እንዳሉኝም አደርጋለሁ። በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ፈረስዎ በእኛ ቋንቋ እንዲናገር አደርገዋለሁ" ሲል ቃል ገባ።ንጉሡ በዚሁ አሰናበቱት። ያ ሊቅ ምሁር ከንጉሡ እንደተለየ ከአንድ ብልህ ወዳጁ ጋርይገናኛል።ለዚህ ወዳጁ ለንጉሡ ስለገባው ቃል አጫወተው። ወዳጁም፡-"ሰማህ ወይ እንደዚህ ያለ እብደት እንዴት ትፈጽማለህ? ፈረስ ቋንቋ ሲማር ያየኸው የት አገር ነው? ንጉሥ አስደስታለሁ ብለህስ እንዴት አንገትህን ለሰይፍ ታመቻቻለህ? ከእንዳንተ ያለ ሊቅአዋቂ ይህንን አልጠብቅም" ይለዋል።

ሊቁ እንዲህ ሲል መለሰ፡-"ወዳጄ እኔም አስቤበታለሁ። የንጉሡን ትዕዛዝ የተቀበልኩት ለምን መሰለህ? በእኛ አገርእስከ አምስት ዓመት ድረስ የሚሆነው ምን ይታወቃል? ወይ ንጉሡ ይሞታሉ። ወይ እኔ እሞታለሁ። ወይ ፈረሱ ቋንቋ ይማር ይሆናል!"

በነሲብና በአቦ ሰጡኝ፣ ተስፋ በመቁረጥና ንጉሥ ለማስደሰት ብሎ ከህሊናው ውጭ የማይሆነውን ይሆናል የሚል የተማረ ዜጋ አይጣል ነው። እንዲህ ያለው ምሁር የሀገር እዳ እንጂ የሀገር መድህን አይደለም። አገራችን እንኳን የነሲብና የ"ጥንቆላ" መላምት ተጨምሮባት እንዲያውም እንዲያው ናት። የዛሬ ሃያ ዘጠኝ ዓመት ግድም አንድ ለብዙ ጊዜ ውጭ ሀገር የቆዩ ኢኮኖሚስት አዛውንት "የሀገራችን ኢኮኖሚ ሁኔታ ምን ይመስለዎታል?" ሲል አንድ ወጣት ቢጠይቃቸው፤ "አይ ልጄ እንዲያው ባጠቃላይ ይሕቺ ሀገር'ዲካርቴ' ገብታለች ለማለት ይቻላል።" ብለው ነበር። እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደር ነው የአዛውንቱ ጨዋታ። ምሁራን በሹመት ከተደለሉ፣ ግለኝነት ካጠቃቸውና የዘለቄታውን ሳይሆን የእለት የእለቱን ብቻ የሚያዩ ከሆነ፣ "ፈረሱ ቋንቋ ይማር ይሆናል" ከማለት የተሻለ ሚና አይኖራቸውም። ተደናግረው ከማደናገር፣ በአእምሮአቸውም፣ በአካላቸውም፣ ሙስናውስጥ ተዘፍቀው፣ አሉ እየተባሉ ቢንከላወሱ፣ "አያድን ጋሻ ቂጥ ያስወጋል" እንዲሉ፣ ለሀገርም ለህዝብም ሳይበጁ መቅረታቸው ነው።

አልበርት ካሙ እንዳለው፤ "ምሁር ማለት አዕምሮው ለራሱ ዘብ የሚቆምለት ሰው ነው። መልካም ራዕይ ያላቸው ምሁራን ለሀገር ያስባሉ። ለህዝብ ይቆረቆራሉ። ይህን ለመፈጸም ከሁሉ አስቀድመው ለአካዳሚው ህብረተሰብ ሰብዕናና መብት መከበር ያስባሉ። ለሙያ ክብር ይቆማሉ። እንዲያም ቢባል ለሙያቸው ተቀዳሚነትና ህልውና ማሰብ ብቻውን አያጸድቅም። የሙያቸው ህልውና መታወቁ ዋና ጠቀሜታው በተግባር ሥራ ላይ አውለው እራሳቸው ተጠቅመው ህብረተሰባቸውን ሲያገለግሉበት ነው። ያኔ ለሀገር የሚበጅ እሴት ይሆናሉ። ለሙያ መታመን ታላቅ ህሊናዊ ኃላፊነት ነውና በማናቸውም መንገድ ቀዳሚውና ክብሩ ጉዳይ እሱ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችል ተጠቃሽ አደጋ ግን አለ- የሙያ- ተአብዮ (Intellectual Arrogance)። የሁሉ ዳኛ የሁሉ ችግር ፈቺ እኔ ነኝና አንቱ በሉኝ፤ እንደመካኒክ ሻንጣ ተሸከሟችሁኝ ዞሩ። ለሁሉ ችግር እኔ ነኝ መፍቻው፤ ሁሉ ሀገር እኔ ልሂድ፤ ሁሉ ሀሳብ ከኔ ይምጣ የማለት አባዜ ሲጠናወት ደግሞ ይብስ ይጎዳል። በተደጋጋሚ የተከሰተው ዛሬም ያልጠፋ ቀንደኛ ችግራችን ነው።

ሌላው በሰራው ድንገት ብቅ ብሎ ሹመት ሽልማቱን ልቋደስ ማለቱም ሌላ ጣጣ ነው። በፖለቲካው ትግል አንፃርም ቢሆን በልባዊነትና በልባምነት የደከመው እያለ "የለውጥ አርበኛ" መሆን፣ የ"ለውጥ ሐዋርያ" መሆን፣ "አዲስ ግልብጥ" መሆን፣ "የነቃ የበቃ" ካድሬ መሆን፣ ጮማ ምሁር ነኝ ከማለት (Crean of the intelligentia) ጋር በእብሪት ሊተሳሰር ሲሞክር አደጋው የዛኑ ያህል የግለኝነት ጥንስስ እንዳለበት አመላካች ነው። "አርሶ እህል ያደረሰ መቆፈሪያ ግድግዳ ላይ ሲሻጥ፣ ግድግዳ ላይ የነበረ ማንኪያ ምግብ ላይ ይቆማል" እንደሚለው የወላይታ ተረት መሆኑ ነው።

የሀገር ጉዳይ ያገባኛል የሚል ምሁር ችግሯን መጋራት፣ መፍትሔዋን መፈለግና ማፋለግ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሙያን ለመለገስ ንፉግ አለመሆን ይኖርበታል።መማር አዲስ ነገርን ለመቀበልም ሆነ ለመስጠት አዕምሮን መግራት ነው። የታነጸ አዕምሮ ያለው ዜጋ ችግሮችን አስቀድሞ የመረዳት፣ መፍትሔዎችንም ፈጥኖ የመሰንዘር ብቃት ይኖረዋልና ለሀገር ጉዳይ ምሁሩ ቅርበት አለው የሚባልበት ሁነኛ ምክንያቱ ይህ ነው። እንጂ አካዳሚክ አባ-ወራነት ብቻውን የሀገሩ "ባለቤት"፣ የሕዝቡ "ጌታ" አያደርግም። የአካዳሚ መሳፍንትነት (Accadamic aristocracy) ወደ ማንአለብኝነት ስርዓት እንጂ ወደ ጤናማ ዲሞክራሲያዊ የእውቀት አምባ አያመራም። ከሁሉም በላይ ከምሁሮቻችን የሚጠበቀው ከስንዝር ወዲያ ክንድ ማሳየት ነው። የቅርቡን ዳገት ሳይሆን ከጀርባው ያለውን ገደልወይም ሜዳ መጠቆምነው። በነቢብ የሚነገረው በገቢር ምን ይሆናል ብሎ መተርጎም ነው። ሁሌም አንድ እርምጃ ቀድሞ የያዝነው መንገድ ወዴት ያደርሰናል ማለት ነው።

"የአህያ ጆሮ ቆሟል ዝናብ ይመጣል" ከሚል ግምት እንድንላቀቅ ማገዝ ነው። "ንፋስ በዛ ትልቅ ሰው ይሞታል" ከሚል መላ ምት ወጥተን ትክክለኛውን የአየር ጸባይ የመገመት፣ የህብረተሰብ ሳይንስን መሰረት ያደረገ ትንተና የመጠቀምመላ እንድንጨብጥ ማመላከት ነው።

ለምሳሌ የዩኒቨርስቲው የወደፊት ራዕይና እጣ ፈንታ ምንድን ይሆን፣ የክልል ፖለቲካናየሊብራሊዝም ዝምድና ከየት ወዴትስ (Cause, process and effect) ምንድን ነው፣ "ዳሩ ሲነካ መሐከሉ ዳር ይሆናል" ማለት ለስልጣነ- መንበሩ ያለው ትርጓሜ ምንድን ነው? ወዘተ የሚሉትን ሐሳቦች የሚያሳይ አብይ ትንተናና ፋና ወጊ ሐሳብ መስጠት እንጂ በትናንሽ ስልጣን ኮርቻ ዙሪያ ተቀምጦ በጉዳይ አስፈጻሚነት ከአፍንጫ ያልራቀ ወይም እስከ አፍንጫም ያልደረሰ አስተያየት ቢሰጡ፣ "ይሄ ሳር ፍለጋ ዱባ ለመስረቅ ነው" ከማሰኘቱ ሌላየምሁር ንፍቀ ክበብ ደንብና ወግ አይሆንም።

"ምሁር የማስጠንቀቂያ ደወል ነው" እንዲል መጽሐፉ፤ በእውቀቱ የሕብረተሰብ ቃፊርነቱን ማሳየት ይገባዋል። እንቅስቃሴ- አልባ መሆን (Non-Dinamic) ወይ በምቾት ከመስባት፣ ወይ በወሬ ከመትባትና ከመተበት አሊያም ያለውሉ ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ ከማረጥረጥ ያለፈ ሚና አይኖረውም። ይሄው እንዳይበቃው ይህንኑ ለመሸፈን ሲል ስሜን ያስነሳል ለሚለው አንዳች ረብ- የለሽ ጉዳይ ዙሪያ አውሎ ነፋስ ማስነሳትን ስራዬ ብሎ ይያያዛል። "የመቀመጥ ብዛት የደረቀ ቁስል ያስፍቃል" ይሏል ይሄ ነው። ይሄ በሁሉ ሰፈር፣ በሁሉም ካምፕ፣ በሁሉም ጎራ፣ በመጤው፣ በፖለቲከኛው፣ በባለሙያው ዘንድ መታየቱ ጉዳዩን የበለጠ አሳሳቢ ያደርገዋል። ኋላ አቧራው መሬት ሲወርድና ንፋሱ ሲቆም ከተቀመጠበት ፎቀቅ ያላለ ምሁር መኖሩ ይፋ መሆኑ አይቀርም። ሕዝቡም እንደፈረደበት እንደዘፋኙ "ቃልሽን ያንቆርቁረው በቀለመ-ወርቁ እኔ አንቺን ስጠብቅ እየተኙ ነቁ" በማለት ወቅታዊ ጥሪውን ማቅረቡን ይቀጥላል።

## አጀንዳ

# ኮሌጅ ስለገባህ ብቻ ራስህን አትለውጥም !

ትምህርት ጥሩ ነው። ኮሌጅ መግባትም አሪፍ ነው። ግን ኮሌጅ ስለገባህ ብቻ እራስህን ትለውጣለህ፣ ሀገርን ትቀይራለህ ማለትም አይደለም። በሀገራችንም ፊደል ከመቁጠር ውጭብዙ ትምህርት የሌላቸው፣ ሆኖም በተፈጥሮ ባላቸው ችሎታ ስኬታማ የሆኑ ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡

ወደ ውጭም ስንሄድ ታዋቂው የአቶሞቢል አምራች የፎርድ ኩባንያመሥራች የሆነው ሔነሪ ፎርድ፣ አይደለም ኮሌጅ መግባትመደበኛ ትምህርቱን እንኳን በወጉ ማጠናቀቅ ያልቻለ ሰው ነበር። ልክ 15 አመት ሲሆነው ትምህርቱን አቆመ። ሆኖም ህልም ነበረው። ያ ህልሙን ያለ አንዳች የመደበኛ ትምህርትና የኮሌጅ ዲግሪ ማሳካት ቻለ፡፡

አዶልፍ ዳስለርምእንደዛው ነው። ዝነኛው የስፖርት ትጥቅ አምራች የአዲዳስ ባለቤት ከሁለተኛ ደረጃየዘለቀ ትምህርት አልነበረውም። ሆኖም የኮሌጅን በር አለመርገጡ፣ በአለም ዝነኛ የሆነውን አዲዳስን ከመመስረት አላገደውም። ስለዚህ ተማሪዎች ኮሌጅ ቢገቡ፣ ቢማሩ ጥሩ ነበር፤ ሆኖም በወደቀው የትምህርት ፖሊሲናበተለያዩ ምክንያቶች ይህን አላሳኩምና፣ እንደ እርባና ቢስመቁጠር ትክክል አይደለም። ማን ያውቃል፣ ወደፊት ሀገራችንን የሚለውጡት ዛሬ የኮሌጅ መግቢያ ውጤት ማምጣት ያልቻሉ ተማሪዎች ይሆናሉና፣ለአእምሯቸው እንጠንቀቅ።

(ዋሲይሁን ተስፋዬ)

የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ በየሳምንቱ የሚታተም **ሚያዚያ 21/1996 ዓ.ም** ተጀመረ

ረቡዕ - ጥቅምት / 28 / 2016 ዓ.ም

ድሬ ጋዜጣ

**አዘጋጆች**
በጽሎ ኃይሌ
ማቲያስ እንዳለ
እስክንድር ኡስማን

**ፎቶ ግራፈር**
ሰላም አበበ

**ዋና አዘጋጅ**
ሔለን ሽጉጤ
( 09 20 26 49 55 )

**ሌይአውት ዲዛይን**
ሰማን ሙስጠፋ

**የኮምፒዩተር ፅሁፍ**
ዘነቡ ፋንቱ

ስልክ - 025 111 6065
ፋክስ - 025 111 4972 ፖ.ሳ.ቁ 370
ኢ-ሜይል - Info pubbure@yahoo.com
ዌብሳይት - www.direcomm.gov.et
ፌስቡክ - Dire Dawa Geovernement Communication Affairs Bureau (@DDGCAB)

# በአስተዳደሩ የትምህርቱን ዘርፍ ለማሻሻል የተጀመሩ ስራዎች በ2016 በጀት አመት ይበልጥ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተገለፀ

የድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሱልጣን አልይ በ2016 በጀት አመት የዝግጅት ምዕራፍ በቢሮው የተከናወኑ አንኳር ስራዎችን እና በትግበራ ምዕራፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት የሚሰሩ ስራዎችን መተመለከተ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል።

በመግለጫቸውም እንደተቋም በ2016 በጀት አመት የዝግጅት ምዕራፍ ከተሰሩ ስራዎች መካከል ከመደበኛ የእቅድ ዝግጅትና ተያያዥ ስራዎች ባለፈ የክረምት ወራት በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሀ-ግብር እና በሌሎች የበጎ አድራጎት ተግባራት የተሰሩ ዋና ዋና ተግባራትን በዝርዝር የገለፁ ሲሆን በዚህምበደም ልገሳ መርሀ-ግብር በሰው 7 ዩኒት፣ ለአረጋውያን እና አቅመ ደካሞች ድጋፍ የሚውል 2 ኩንታል የወንድና የሴት አልባሳትና ጫማዎች ፣ 200 ኪ.ግ ሩዝ እና አራት ሙክት ፍየሎች በአጠቃላይወደ መቶ ሀያ ሺ ብር ግምት ያለው ድጋፍ መደረጉን ነው አቶ ሱልጣን አልይ የገለፁት።

በ2016 የትምህርት ዘመን ትምህርት ቤቶችን ለመማር ማስተማር ምቹ ከማድረግ አንፃርስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ብርወጪ በማድረግ በ 9 ትምህርት ቤቶች ማለትም በ 4ቱ ትምህርት ቤቶች የሽንት ቤት ግንባታ እና በ 5ቱ ደግሞአዲስ የሽንት ቤት ግንባታ መከናወኑን የገለፁት የቢሮ ኃላፊው ከዚህም በተጨማሪ በአስራ አምስት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺ ብር በላይ በሆነ ወጪ የ16 መማሪያ ክፍሎች እድሳት እና የ3 መማሪያ ክፍሎች አዲስ ግንባታ ተከናውኖ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን ተናግረዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በቀጣይ የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሻለ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ በአስተዳደር ተዘጋጅቶ በነበረው የትምህርት ለትውልድ መርሀ_ግብር ማስጀመሪያ መድረክ ላይ የተለያዩ ባለሀብቶችየገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ቃል መግባታቸውን የገለፁት አቶ ሱልጣን በዋናነትም በማሪያም ሰፈር ትምህርት ቤትለሽንት ቤት ግንባታ የሚውል 753,000 ብር፣ በ06 ወረዳ የቅድመ አንደኛ ኬጂ መማሪያ ክፍሎች ግንባታየሚውል 2,000,00 ብር እና በጎላደግ ትምህርት ቤት ለቅድመ አንደኛ ኬጂ መማሪያ ክፍሎች ግንባታየሚውል 1,500,000 ብር አጠቃላይ አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀምሳ ሶስት ሺ ብር የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም ለተማሪዎች ምገባ ድጋፍ የሚውል አስራ ሰባት ሚሊዮን ብር ከናሽናል ሲሚንቶ አክሲዮን ማህበር ቃል መገባቱን አቶ ሱልጣን ተናግረዋል፡፡

አቶ ሱልጣን አክለውም አቅም ለሌላቸው ተማሪዎች የትምህርት ግብዓቶችን ለማሟላት የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦችን በማስተባበር



10,828 ደርዘን ደብተር፣ ብዕር በፍሬ 56,774፣ እርሳስ በፍሬ 4,668፣ ቦርሳ በፍሬ 1,190፣ የተማሪ የደንብ ልብስ 370 በአጠቃላይ በገንዘብ ሲተመን አጠቃላይ ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር ግምት ያለው ድጋፍ መሰብሰቡንም ነው የገለፁት።

አጠቃላይ የ2015 የትምህርት ማጠቃለያ የ8ኛ ክፍል እና የ12ኛ ክፍል የተማሪዎች የፈተና ውጤትን በተመለከተም የቢሮው ኃላፊ በሰጡት መግለጫ የ8ኛ ክፍል ማለፊያ ውጤት 40% ፐርሰንት መደረጉን ገልፀው በዚሁ መሰረትምበትምህርት ዘመኑ ለፈተና የተቀመጡ ተማሪዎች ቁጥር7345 መሆኑንና ከነዚህ መካከልም የማለፊያ ነጥብ ያመጡት 2815 (38%) መሆኑን ፤ በተመሳሳይ የ12ተኛ ክፍል መልቀቂያላይ ለፈተና የተቀመጡ ተማሪዎች ቁጥር 4729 መሆናቸውን ከነዚህም መካከል የማለፊያ ነጥብ ያመጡ 213(4.5%) እንደሆኑ እና በቀጣይ የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች እውቅና የመስጠት መርሀ-ግብር የሚኖር መሆኑን ተናግረዋል።

አዲሱን ስርዓተ ትምህርት መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ እናየታተሙመማሪያ መፅሀፍትንበተመለከተምበአጠቃላይ 204 መማሪያ መፅሀፍት መዘጋጀታቸውን አቶ ሱልጣን የገለፁ ሲሆን ከነዚህ መካከልም 129 መፅሀፍትበ3ቱም ቋንቋዎች ተዘጋጅተው መታተማቸውን ቀሪ 75 መፅሀፍትን ለማሳተም ደግሞ በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልፀው በአጠቃላይ የ2016 በጀት አመት በአስተዳደሩ የትምህርቱን ዘርፍ ለማሻሻል የተጀመሩ ስራዎች ይበልጥ ተጠናክረው የሚቀጥሉበት አመት እንደሚሆን እና ለስኬታማነቱም ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸው ሁሉ በአግባቡ እንዲወጡም የድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሱልጣን አልይ መልዕክት አስተላልፈዋል ሲል ዘገባውን ያደረሰን የቢሮው ህዝብ ግንኙነት ክፍል ነው።

# የመንግስት ግንባታ ፕሮጀክቶች የክትትልና ቁጥጥር ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉ ተገለፀ

የድሬዳዋ አስተዳደር በየዓመቱ በሚመድበው በጀት የሚሰሩ የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶችን ጠቀሜታና የሚቀርፏቸውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በተመለከተ ማብራሪያ የሰጡት የድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ምክትል ሃላፊ የሆኑት አቶ ደራራ ኢብራሂም በአስተዳደሩ የሚገነቡ የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶችን ጠቀሜታና የሚቀረፉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በቢሮው የተቋቋመው የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች የክትትልና ቁጥጥር ቡድንየድጋፍ፣ የክትትልና ቁጥጥር አገልግሎት የሚሰጣቸውን የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች በጎበኙበት ወቅት ቢሮው ለመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሂደትና አፈፃፀም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የክትትልና ቁጥጥር አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን አሳውቀዋል፡፡ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው መርሃ ግብርና በጀት ተጠናቀው ለታለመላቸው አላማ እንዲውሉ እየተሰራ ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ሃላፊው እየተገነቡ



የሚገኙት የአስተዳደሩ የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች የድሬዳዋን ራዕይ የሚያሳኩ ብቻ ሣይሆኑ የድሬዳዋን የምሥራቅ ኢትዮጵያ ፈርጥነት የሚያረጋግጡም ናቸው ብለዋል፡፡

የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች የቴክኒካል



ሱፐርቪዥን ቡድን የክትትልና ቁጥጥር አገልግሎት ተጠናክሮ መቀጠሉን የተናገሩት ደግሞ ኢንጂነር ኢየሩሳሌም አየለ ሲሆኑ በማብራሪያቸውም በድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች ቴክኒካል ሱፐርቪዥን ቡድን የተቋቋመው በአስተዳደሩ የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሂደትና አፈፃፀም ላይ ያጋጠሙ የግንባታ ጥራት መጓደል፣ የመዘግየት ወይም የመጓተት፣ አልፎ አልፎም የመቋረጥና አላስፈላጊ የበጀት መጨመር ችግሮችን ለመቅረፍ ነው ፡፡

ኢንጂነር ኢየሩሳሌም አየለ ስለቴክኒካል ሱፐርቪዥን ቡድን አገልግሎትና ስለተገኙ ውጤቶች ሲገልጹም፤ በአሁኑ ወቅት በግንባታ ላይ ለሚገኙ የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች የድጋፍ፣የክትትልና የቁጥጥር አገልግሎት ሰፊ ስራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ ቴክኒካል ሱፐርቪዥን ቡድኑ ከተቋቋመ ጀምሮ የተከናወኑ ተግባራትንና የተገኙ አበረታች ውጤቶችን የተናገሩት ኢንጂነር ኢየሩሳሌም ካለፉት ዓመታት የተሻለ አጥጋቢ ውጤት ለማስመዝገብና በመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ በዘንድሮው ዓመትም በተጠናከረ ሁኔታ የክትትልና የቁጥጥር አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን አስረድተዋል ሲል የዘገበው የቢሮው ህዝብ ግንኙነት ክፍል ነው፡፡

# “እንቅልፌን መለሳችሁልኝ!!”

## በወረዳ 3 በክረምት ወራት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ቤት የተገነባላቸው እናት

የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን በወረዳ 3 በክረምት ወራት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ያስገነባቸውን ሁለት ቤቶች ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሀር እና ምክትል ከንቲባ ሀርቢ ቡህ እንዲሁም ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት ለሁለት አቅመ ደካማ እናቶች አስረከቧል።

በወረዳ ሶስት በተለምዶ አጠራር ገንደ ሮቃ መንደር የሚገኙት ወ/ሮ ዘነበች ከበደ ቀደም ሲል ከነበሩበት ግማሽ ጎኗ ተከፍቶ ከጣሪያ ዝናብ በምታስገባ አመሻሹን የጅብ እራት እንዳልሆን ሲሉ ከሚሰጉባት ቤት ተላቀው በአስተዳደሩ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን በክረምት በጎ ፈቃድ በተገነባላቸው ቤት በረንዳ ዛሬን የሀዘን ሳይሆን የደስታ እንባን እያነቡ እንግዶቻቸውን ለመቀበል በተዘጋጁበት ቀን ነበር ያገኘናቸው።እርሳቸው ያያለፈ መከራቸው በተገነባላቸው ቤት ላይመለስ ተሸኝቷል።

ሌላዋ የነምበርዋን እናትም ከወራት በፊት ከጎሮቤት ተጠግተው ዝናብ ሲመጣ በደከመ አቅማቸው ተሯሩጠው እቃቸውን ለማትረፍ ይጣጣሩ እንደነበር አጫውተውን ዛሬን ግን መንግስት ለረጅም አመታት የራቀኝን እንቅልፌን መለሰልኝ ብለዋል ለተደረገላቸው





በማመስገን።

“በጎነት ለኢትዮጵያ ከፍታ” በሚል እንደ አስተዳደር በክረምት በጎ አገልግሎት አማካኝነት በከተማ እና በገጠር አንድ መቶ የአቅም ደካማ ቤቶችን ለመገንባት እቅድ ተይዞ ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን በአስተዳደሩ ከሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች መካከልም የአስተዳደሩ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲከስ ባለስልጣን ወ/ሮ ዘነበችን ጨምሮ የሁለት አቅመ ደካማ ቤቶችን በመገንባት አስረክቧል።

በስፍራው ተገኝተው ቤቶቹን ያስረከቡት ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሀርም ቤቶቹ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ ሀሳብ አመንጭነት በመላ ኢትዮጵያ እንደመንግስት በእቅድ ተይዘው በሁሉም ሴክተሮች መገንባታቸውን አውስተው፤ እንደ አስተዳደርም አቅም በፈቀደ መጠን የእናቶችን እና አቅመ ደካሞችን እንባ ለማበስ ጥረት ተጀምሯል ይህም በቀጣይ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

ቤቶቹን ከቀበሌው ጋር በመቀናጀት በራሱ ሰርቶ ያስረከበው የአስተዳደሩ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲከስ ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ ክብርት ወ/ሮ ሰአዳ አዋሌ በበኩላቸው ተቋሙ ከመደበኛ አገልግሎቱ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የጃፓን የብልፅግና መንገድ

በስንታየሁ እንግዳ

ሀገሬ በዘመኗ ያሳለፈቻቸው የውጭና የውስጥ ጦርነቶች፣ የረሃብና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ተዳምረው እያንሳቀሏት አሁን ላለችበት ደረጃ ላይ ደርሳለች፡፡ በዚህ ሁሉ ችግርና ውጣ ውረድ ውስጥ ግን ትጠፋለች ያሏት እንደ ተንሸዋረረው እየታያቸው ሳይሆን ሊያጠፏት የማሱላትን ጉድጓድ እየደፈነች አንዳንዶች ጠላቶቿን ደግሞ በቆፈሩት ጉድጓድ እየቀበረች ኢኮኖሚዋን ማሳደግ ባትችልም ነፃነቷን እያስጠበቀች ለራሷ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካዊያን የነፃነት አርማ ሆና ዛሬ ላይ ስለ ባርነት ለሚያወሩልን ቀኝ ገዢዎች ነፃነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከገዛ ታሪኳ መዛ እየነገረቻቸው ኩራቷን ተከናንባ በድህነት እንደሁ እንጂ በጦርነት ተሞክሩ ቀኝ ግዛቶች እጅ አልሰጥም አሻፈረኝ እያለች ኖራለች፡፡

ኢትዮጲያዬ ለበርካታ ዓመታት ያደገች ሳትባል ለማደግ ከሚያኮበኩቡት ተርታ እራሷን ስትመድብ በመቆየቷ አሁንም በኛ ዘመን ካደጉቱ ሳይሆን ወደ መካከለኞቹ ተርታ ለመሰለፍ ቋጥኝ የመቧጠጥ ያክል ትግል ላይ ነች፡፡ ለዚህ ትግል ምክኒያቱ ደግሞ በአንድ ልብ አሳቢና በአንድ ቃል ተናጋሪ ባይኖር እንኳን በተቀራረበ ሁኔታ ሃሳብ ለሃሳብ ተቋድሶ ከአዕምሮ ጥልቀት ውስጥ የሚበጀውን ቆፍሮ በማውጣት ለሀገር ዕድገት መጠቀም ዘንድሮም ኢትዮጲያዬ ብርቅ እየሆነባት ነው፡፡ ትችት ሀገር አያሳድግም፤ ትችት ሆድ አይሞላም፤ ትችት ለልጆቻችን የምናወርሰው ሃብት አይሆንም ብሎም አሉታዊ ትችት አስተማሪና ሚዛናዊ ካልሆነ እንደው በጭፍን ሀገር ማፍረሻ መዶሻ ነው፡፡ እናም ለማደግ ስንጠራራ በቁመታችን ልክ አብሮን ያላደገው አስተሳሰባችን እየኮረኮመን ወደ ኋላ እንዳይመልሰን ልባችንን አስፍተን ለጋራ አብሮነትና ሀገራዊ ዕድገት እንትጋ፡፡ ደሞም ከሰለጠኑቱ እንዴት እንደሰለጠኑ፤ ወደኋላ ከቀሩት ደግሞ ለምን ወደኋላ እንደቀሩ ግራ ቀኝ አይተን የሚበጀንን እንከተል፡፡

በአጭር ጊዜም ይሁን በረጅም ጊዜ እልህ አስጨራሽ ጉዞ በኋላ ወደ ስልጣኔና ዕድገት ማማ የወጡት ሀገራት ከሳቱበት እየተመለሱ፤ ከወደቁበት እየተነሱ ደምም ከችግራቸው እየተማሩ ዛሬ ያሉበት የዕድገት ጫፍ ላይ አሉ፡፡ ሳይወድቁ መነሳት፤ ሳይማሩ ማወቅ፤ ሳይሳሳቱ መታረም እና እታች ሳይሉ እላይ ስለሌለ ሀቁን ተጋፍጦ ፅኑአን መሆን ለሀገሬ የሚበጃት እውነት ነው፡፡ «ሞያ ከጎረቤትን» ይላልም አይደል የሀገሬ ሰው፡፡ እኔ ደሞ ዛሬ ከጎረቤት ሳይሆን በርካታ ማይሎችን አቋርጬወደ ስልጡኗ ጃፓን አቅንተን ከዘመናቶቿ ዘመንን ተሻግረን ከችግሯና ከስኬቷ ለኛም ለትምህርታችን ይሆነን ዘንድ ጥቂት ጉዳዮችን እንመለከታለን፡፡

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ጃፓን ኢኮኖሚዋ በግብርና ላይ የተመሰረተ፤ አነስተኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ፤ በአጠቃላይ ኋላቀር እንዲሁም በወቅቱ ኃያላን በነበሩት በምዕራባዊያን ተፅዕኖ ስር የወደቀች ሀገር ነበረች፡፡ ሆኖም ኢኮኖሚዋን ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር ባደረገችው ከፍተኛ ጥረት ስኬታማ ለመሆን በቅታለች፡፡ ምዕራባዊ ካልሆኑ ከሌሎች ሀገራት ተለይታ ጃፓን በቀዳሚነት ለምን ተሳካላት የሚለው ጥያቄም በጃፓን ዘመናዊ ታሪክ ላይ ጥናት ለሚያካሄዱ ሁሉ ወሳኝና መሰረታዊ ጥያቄ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ዶ/ር ታዳአ ኡሚሳአ የተሰኙ ታዋቂ ምሁር ጃፓን ቀድማ ስኬታማ መሆኗ የተለየ ሚስጥር የለውም፡ ፡ይልቁንም በሂደት የመጣ እንጂ፡፡ ከምዕራባዊያን ውጭ የጃፓን ስልጣኔ ሊከሰት መቻሉ ተፈጥሮአዊ ነው ይላሉ፡፡

ጃፓንና ምእራብ አውሮፓ ከታላቁ የኤሮኤዢያ ሀገሮች (ከቻይና፣ ህንድ፣ ከመካከለኛ ምስራቅ) እምብዛም ያልራቁና ያልቀረቡም በመሆናቸው ከእነዚህ ሀገራት ስልጣኔ ጠቃሚ ባህሎችንና ክንዋኔዎችን ተጋርተዋል፡፡ በኤሮኤዢያ እምብርት ላይ እንዳሉት ሀገራት የበረታ ባይሆንም ጃፓንና ምዕራብ አውሮፓዊያንም ቢሆኑ በወቅቱ በስልጣኔ በገነኑት ሀገራት ወረራና ጥቃት ተፈፅሞባቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በሁለቱ ማህበረሰቦች በጥቅልና ከውስጥ በመጣ ዕድገት እንዲያልፉ ረድቷቸዋል፡ ፡ ምክኒያቱም ማህበረሰቦች ነባሩን ባህላቸውን አጥፍተው በአዲስ አልተኩም፡፡ ይልቁንም የውስጡን ባህል ከውጪ ከመጣው ጋር በተገቢው አዋህደው ተጠቅመዋል፡፡

ይህን ተመሳሳይ ታሪካዊ ሁነት የተጋሩት ጃፓንና ምዕራብ አውሮፓም በየግላቸው በራሳቸው መንገድ ለማደግ ችለዋል፡፡ ከማዕከላዊ ኢምፔሪያሊዝም እስከ ኢ-ማዕከላዊነት፤ ፊውዳሊዝምን ቀጥሎም ፍፁማዊነት






በመጨረሻም ካፒታሊዝም ሁለቱም ያለፉባቸው የዕድገት ደረጃዎች ናቸው፡፡ የኢንዱስትሪ አብዮት በዩናይትድ ኪንግደም በድንገት አልተከሰተም፡፡ ጃፓን ደግሞ ከምዕራቡ ዓለም ውጭ የኢንዱስትሪ አብዮትን ያካሄደች ብቸኛ ሀገር ነች፡፡ ይህ ዓይነት የታሪክ መመሳሰል በሌላ በማንም ሀገር አልታየም፡፡ እንደ አሚሳአ እምነት ሁለቱ ሀገራት ማለትም ጃፓንና ዩናይትድ ኪንግደም በአንድ ጊዜ የኢንዱስትሪ አብዮትን አካሄደዋል፡፡ የቻይና፣ ህንድና የአረቡ ዓለም ሥልጣኔ ጉልህ የባህል ለውጥ ስኬትን ያስከተሉ ቢሆንም ምንም ዓይነት ሥርዓተ ማህበራዊ ለውጥ ማምጣት ግን አልቻሉም፡፡ ንጉሳዊ አምባገነናዊ አገዛዙ እንደነበረው ቀጥሎ የኋላ ኋላም ሀገሮቹ ለቀኝ ግዛት ተዳርገዋል፡፡

እነዚህ ሀገሮች ከአንዱ ስርወ መንግስት ወደ ሌላው በሚያደርጉት ሽግግርም ምንም ዓይነት ማህበራዊና ፓለቲካዊ ለውጥና መሻሻሎች አላሳዩም፡፡ ለአንድ ሺህ ያህል ዓመታት የነበሩት ነገስታትም አንድ ዓይነት ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ እንደ ኡሜሳኡ አባባል ለኢንዱስትሪላይዜሽን አስፈላጊ የሆነውን የታሪክ ቅድመ ሁኔታ በተገቢው አሟልተው ያለፉ ሀገሮች ምዕራብ አውሮፓና ጃፓን ብቻ ናቸው፡፡ ምናልባት ሰሜን አሜሪካ እንደ አንድ የምዕራብ አውሮፓ ክፍል ልትታይ ብትችልም ጃፓን ግን የምዕራባዊያኑን የዕድገት ሂደት በፍፁም በቀጥታ አልቀዳችም፡፡ ጃፓን ሆነች ምዕራብ አውሮፓ እንደራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በተናጥል ለዕድገት በቅተዋል፡፡

ውድ አንባቢዎቼ እስቲ አሁን ደሞ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስኬቶች መካከል ያሉ ክፍተቶችን እንቃኝ፡-

የማህበራዊ ሳይንስ ባለሞያው ኬኒቺ ቶሚንጋ «የጃፓን ዘመናዊ ስልጣኔና ማህበራዊ ለውጥ» በተሰኘው መፅሐፋቸው ስለጃፓን ሥልጣኔና በኢንዱስትሪ እንዴት ለመበልፀግ እንደበቃች አብራርተዋል፡፡ የጃፓንን የቅርብ ታሪክ በተመለከተ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ሁለት አተያዮች ይነሳሉ፡፡ የመጀመሪያው የጃፓን ስኬትና በተለይም ከምዕራባዊያን ጥቂት ዘግይታም ቢሆን ለዕድገት መብቃቷን የሚቃኝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የቀድሞዋ ጃፓን የገዛ ሕዝቦቿን ጨቋኝ፤ ጎረቤቷቿንም ወራሪ እንደነበረች ያወሳል፡፡

በእርግጥ ጃፓን ለታዳጊ ሀገራት አብነት/ ምሳሌ የምትሆን ሀገር ናት ወይስ በምንም መልኩ ልትጠቅም የማትችል የሚል ክርክር አንዳንዴ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ እንደ ቶሚንጋ አባባል ዘመናዊ ስልጣኔ በሳይንሳዊ እሳቤ እና ሞዴል ሊተነተን የሚገባው ውስብስብ ክስተት ነው፡ ፡ ቶሚንጋ አፅንዖት የሚሰጡት ምዕራባዊ ያልሆኑ ሀገሮች ወደ ስልጣኔ የሚያደርጉት ጉዞ ምዕራባዊያኑ ያለፉበት መንገድ የሚደገም አይደለም፡፡ በመሆኑም ምዕራባዊ ያልሆኑ ሀገሮች ስኬታማ እንዲሆኑ ወደ ስልጣኔ በሚያደርጉት ጉዞ ነባሩንና የውጪውን ባህል በማነፃፀር አዲስ ፈጠራ ሊያመነጩ ግድ ይላቸዋል፡፡

ባዕዱን ባህል እንደወረደ ሳይሆን እየመረጡ በመቅሰምና ከነባሩ ጋር በማዋሃድ አዲስ ነገርን መፍጠር ማለት ነው፡፡ ታዲያ በነባሩና በመጤው ባህልና አሠራር መካከል አለመጣጣም ከተፈጠረ ማስወገድ ያስፈልጋል፡ ፡ የጃፓን ስልጣኔም ይህንኑ የተከተለ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም የቶሜንጋ ዘዴ ማህበረሰቡን በአራት ንዑስ ስርዐት/መዋቅር በመከፋፈል የእያንዳንዳቸውን ለውጥም በዝርዝር ይቃኛል፡፡

- ኢኮኖሚያዊ ዕድገት /በኢንዱስትሪ በመበልፀግ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት




- ፖለቲካዊ ዕድገት/ዲሞክራሲ
- ማህረሰባዊ ዕድገት/ ዝግ ከሆነው የገጠሩ ማህበረሰብ አዳዲስ ሃሳቦችን ለመቀበል ዝግጁ ወደ ሆነው የከተማው ማህበረሰብ የሚደረግ ለውጥ/
- ባህላዊ ስልጣኔ /ከኢ-ምክኒያታዊ ልማዳዊ እምነት ወደ ሳይንሳዊና ምክኒያታዊ አመለካከት የሚደረግ ሽግግር/

ከላይ የተጠቀሱትና የቶሚንጋ ዋና መከራከሪያም ባጭሩ እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል፡፡ የአውሮፓ ዘመናዊ ስልጣኔ የሚጀምረው የኢንዱስትሪ አብዮቱን ተከትሎ በመጣው በፖለቲካዊና ማህበራዊ ስርዓቱ ውስጣዊ ዕድገት ነው፡፡ሆኖም ግን ዘግይተው ለዕድገት የተነሱት ወይም በማደግ ላይ ያሉት ሀገራት ግን በዚህ ቅደም ተከተል ማለፍ አይችሉም፡፡ ከነሱ ፖለቲካዊ ዕድገት ይልቅ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጣት ይቀላቸዋልና ነው፡፡ ማህበራዊ እና ባህላዊ ዕድገት በማምጣት ወደ ዘመናዊ ስልጣኔ ለመዳረስም ቢሆን እጅግ አስቸጋሪ ነው፡ ፡ ምክኒያቱም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና ኢንዱስትሪን ቀድቶ ከማስተዋወቅ ጋር ሲነፃፀር ከእያንዳንዱ ሰው ህይወት ጋር በእጅጉ ተቆራኝቶ የኖረን ስርዓት መቀየር እጅግ ረጅም ጊዜና ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ ታዲያ ይህ በኢኮኖሚው ፈጣን ዕድገት በማምጣት በአንፃሩ ግን የሌሎች መስኮች ዕድገት አዝጋሚ ይሆናል፡፡

ሆኖም ግን ኢኮኖሚያዊ ስርዓቶች ኢኮኖሚያዊ ካልሆኑት ጋር ተያያዥ በመሆናቸው ይህ ክፍተት ውጥረትንና ግጭትን በመፍጠር ሀገሪቱ ወደ ስልጣኔ የምታደርገውን ጉዞ የተዛባ ያደርገዋል፡፡ ከጦርነቱ በፊት ጃፓን በአንድ በኩል በቴክኖሎጂና በኢንዱስትሪ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰች ቢሆንም በሌላ ጎኑ ደግሞ ቅድስቲቷ ሀገር ከጥንታዊያኑ ነገስታት አምልኮ የምትገኝ ናት የሚለው አስተሳሰባቸውና እንዲሁም የመሳፍንታዊ ስርዓቱ መኖር በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ምንም እንኳን የቶሚንጋ ትንታኔ ዝነኛ ከሚባሉት አንዱ ቢሆንም የራሱ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ የቶሚንጋ ሌላው የመከራከሪያ ነጥብም፡-

ከኢዶ ዘመን በፊት ጃፓን ለዘመናዊ ስልጣኔ የሚያበቃ ምንም ዓይነት መሰረታዊ ሀሳብ ወይም የአመራር ስርዓት አላመነጨችም ነበር፡፡ ዘመናዊ ስልጣኔም የተጀመረው ከሜጂ ዘመን በኋላ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ምክኒያት የሚያቀርቡት ተለምዶዋዊውን ስርዓት ወደ ጎን በመተው ሀገሪቱ ለውጪው በሯን ክፍት ያደረገችበት ጊዜ ነበርና ነው፡፡ እራሱን ከውጪው ዓለም ዘግቶ የሚኖር የገጠር ማህበረሰብ ባለበትና ኢ-ምክኒያታዊ አስተሳሰብ በሰፈነበት ማህበረሰብ ዘመናዊ ሥልጣኔ ሊመጣ አይችልም፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ሳይለወጡ ዘመናዊሥልጣኔ ላይ ቢደረስ እንኳን ውዝግብና ግራ መጋባት መፈጠሩ አይቀሬ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የዘመናዊ ሥልጣኔ ክፍተቶች በጃፓን በቅድመ ጦርነት ይታይ የነበር ቢሆንም ከጦርነቱ በኋላ በተደረገ ማሻሻያ ችግሩ ተወግዶ ዛሬ የምናያትንና ባህሏንና ዘመናዊነትን አጣምራ በመያዝ በኢኮኖሚም ይሁን በቴክኖሎጂው ከቁንጮዎቹ ተርታ የተስተካከለች ጃፓንን መፍጠር ተችሏል፡፡

ውድ አንባቢዎቼ በገንዘብና ኢኮኖሚ ሚንስቴር በ 2005 ዓ/ም የታተመች መጽሔትን መነሻ በማድረግና በበርካታ ሃሳቦች በመጽሔቷ በመታገዝ ሀገራችንም ከታዳጊ ሀገራት ተርታ የምትመደብ ሀገር መሆኗን በማሰብ በጃፓን የዕድገት ጉዞ ሂደት ጫማ ውስጥ የኛን እግር ከተን የሚያመሳስለንና የሚለየንን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚጠቀመንን ወስደን የማይረባንን ትተን እኛም ለዕድገታችን እንትጋ ዘንድ ለጥቅማችን ይህቿን ፅሁፍ እነሆኝ አልኳችሁ፡፡ እናንተም አነበባችኋት፡፡ ህይወት እንደ ግልም ይሁን እንደ ሀገር ብሎም እንደ ዓለም ዓቀፍ በመናበብ፣ በመኮራረጅ፤ አንዱ ዘንድ የሌለን ሌላው በመውሰድና በመስጠት የተቆራኘ በመሆኑ ሀገራችንም ያላትን ሰጥታ የሌላትንና የሚጠቅማትን ወስዳ የዕድገት መንገዷን እንድታቀና በአንድም በሌላ መንገድ ማገዝ የኛ የዜጎቿ ግዴታ ነው፡፡

ሀገር የምታድገው ከትናንት ስህተቷ በመማርና ዛሬን መልካሙን በመሥራት ለነገ ደግሞ የታሻለ ታሪክን በማቆየት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከላይ በመግቢያዬ ለመጠቆም እንደሞከርኩት ምንም እንኳን ብዝሃነታችን የጎላና ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶቻችን የአንዳችን ከሌላው የተለያዩ ቢሆኑም ኢትዮጲያዊነታችን ግን አንድ እንደሚያደርገን ለአፍታም መዘንጋት አይገባም፡፡ እናም ለዚህች ሀገር ዕድገት የሚከፈለውን ዋጋ ከፍለን ወደ ከፍታ ልናወጣትና ለነገ ሀገር ተረካቢዎች የተረፈ ችግር ሳይሆን የተትረፈረፈ ሀብት ልናወርሳቸው ተገቢ እንደሆነ ማሰብ ጠቃሚ ነው፡፡ ለዚህም ነው ጃፓኖችን ለዛሬ ብልፅግናቸው መንገድ የሆናቸውን ምክኒያቶች ማቅረቤ፡፡ ሀገራችንን ፈጣሪ ይጠብቅልን፡፡ የዕድገትና የጤና ዘመን ያድርግልን፡፡ አበቃሁ፡፡

## የቴክኒክና. . .

ከገጽ 1 የዞረ

መርሃግብሩ ይፋ በተደረገበት ስነ-ስርዓት ላይ ኮሌጆቹን የሚመራው የድሬዳዋ አስተዳደር የስራ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሮቤል ጌታቸው እንደተናገሩት፤ መርሃ ግብሩ የተቋማቱን ስኬታማነት ሊገታ የሚችለውን የበጀት እጥረት በመፍታት ተልዕኳቸውን ለማሳካት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

እያሰለጠኑ በማምረት የገቢ ምንጭ ማሳደግ ተቋማቱ የተጣለባቸውን ለሀገር እና በቀጠናው ለሚገኙ ኢንዱስትሪዎችና ተቋማት ብቁ፤ በክህሎት የዳበረ ባለሙያዎች ለማፍራት ያስችላቸዋል ብለዋል። ይፋ የተደረገው መርሃግብር ሀገር በቀል የኢኮኖሚ መሠረትን በማስፋት የኑሮ ውድነትን ለመቀነስም መሠረታዊ ሚና እንደሚጫወት ነው አቶ ሮቤል የገለፁት።

በመሆኑም ይፋ የተደረገው መርሃግብር ውጤታማ እንዲሆን አስተዳደሩ ከሚያደርገው ድጋፍ ባሻገር የባለድርሻ አካላት ተሳተፎ ወሳኝ ይሆናል ብለዋል። የዚህ አይነቱ አስተሳሰብ በሀገር ደረጃ ማምጣት እንደሚቻል ማሳያም ነው ብለዋል፡፡

የድሬዳዋ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ ዳይሬክተር ወይዘሮ ፈጡም ሙስጠፋ በበኩላቸው እንዳሉት፤ መርሃግብሩ በምርምር የሚደግፍ እና የተጀመረውን የሌማት ትሩፋት ውጥን ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም የኑሮ ውድነትን ለማቃለል ያስችላል ብለዋል።

በአዲሱ መርሃግብር ዘንድሮ 12 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት እና በርካታ ወጣቶች የስራ ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ስራው መጀመሩን የገለፁት ደግሞ አቶ ታሪኩ ባይሳ በስራ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የአሰልጣኝ ልማትና የተቋማት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክተር ናቸው።

እንደ አቶ ታሪኩ ገለፃ “እያሰለጠኑ ማምረት፤ እያመረቱ ማሰልጠን” በሚል ይፋ የሆነው መርሃግብር በኮሌጆቹ በብዙ ቢሊዮን ብር የተገዙ የተለያዩ ማሽኖች ወደ ገቢ ማመንጨት ስራ በማስገባት ለስራ አጥ ወጣቶች መፍትሄ ያመጣሉ ያሉ ሲሆን፤ ለመርሀ ግብሩ የሚያስፈልጉ የፋይናንስ አስተዳደር፣ የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ደንቦች ተዘጋጅተው እየተጠናቀቁ ናቸው ብለዋል።

## ለምን ሲሳይ፡- ድንቁ የስነ-ጽሁፍ ሰው

በሔኖክ ይልማ

ነጮቹ ለምን ሲሴ እያሉ ይጠሩታል። በ1950ዎቹ መጨረሻ ላይ ለትምህርት ወደ እንግሊዝ ሃገር የሄደችው የማርእሸት ያልፈቀደችውን ልጅ ታረግዛለች። ልጅ ወልዶ ለማሳደግ ዝግጁ ስላልነበረች የወለደችውን ልጅ 'ለምን' ብላ ሰየመችው። ከዚያም ለምን ሲሳይ በሁለት ወሩ ለማደጎ ተሰጠ።

ከወራት በኋላ የማርእሸት ልጇን ማሳደግ የምትችልበት ደረጃ ላይ ስትደርስ ልጇን መልሱ ብላ አቤቱታ አቀረበች። የማህበራዊ አገልግሎቱ ግን ፍቃደኛ ሳይሆን ቀረ።

ኖርማን የተባለው የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛ ስሙን ከ 'ለምን' ወደ ራሱ ስም 'ኖርማን' ቀየረው። ከዚያም ለነጭ አሳዳጊዎች በማደጎነት ሰጠው።

ወግ አጥባቂ የነበሩት የማደጎ ወላጆቹ በሙያቸው መምህር እና ነርስ ነበሩ። ለምን የልጅነት ጊዜውን ''አስከፊ'' ሲል ይገልፀዋል። በዕድሜ ከፍ እያለ ሲመጣ ለአሳዳጊዎቹ ''አስቸጋሪ'' ልጅ ሆነ።


ምግብ የመብላት ፍላጎት የለውም፣ ወደ ቤት መግባት አይፈልግም፣ በአጠቃላይ በህይወቱ ደስተኛ አልነበረም። 12 ዓመት ሲሞላው አሳዳጊዎቹ ዳግመኛ ልናየው ፍቃደኛ አይደለንም ብለው ለማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች መልሰው ሰጡት።

አስራ ስምንት ዓመት እስኪሆነው ድረስ በአራት የህፃናት ማሳደጊያ ቤቶች ውስጥ ኖሯል። በእነዚያ ዓመታትም በዘር ላይ የተመሰረቱ አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ጥቃቶች ተፈፅመውበታል። ወላጅ እናቱም ጥላው እንደሄደች፤ ወገን እንደሌለው ይነገረው ነበር።

አስራ ስምንት ዓመት ከሆነው በኋላ ስለ እራሱ እና ወላጅ እናቱ የሚያትቱ ጥቂት መረጃዎች ተሰጥተውት ከማደጎ እንዲወጣ ተደረገ። በዚያን ወቅት ነበር ወላጅ እናቱ ''ለምን'' ብላ እንደሰየመችው እና የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛው ስሙን ወደ ኖርማን እንደቀየረ የተረዳው።

እናቱም ለማህበራዊ አገልግሎት ልጇን እንዲመለስላት በፃፈችው ደብዳቤ ''ለምንን እንዴት መልሼ ማግኘት እችላለሁ? ከራሱ ሰዎች ጋር እንዲሆን እፈልጋለሁ፤ አድልዎ እንዲፈፀምበት አልፈልግም'' ስትል እንደተማፀነች የተረዳው። ብዙም ሳይቆይ መጠሪያ ስሙን ከኖርማን ወደ ለምን አስቀየረ።

ለምን ከማደጎ ቤት ከወጣ በኋላ የብቸኝነት ስሜት እጅጉን ይሰማው እንደነበር ይናገራል። ''በበዓላት ወቅት የቤተሰብ አባላት በአንድ ላይ ተሰብሰበው ሲያከብሩ እኔ ግን ብቸኛ ነበርኩ። ለዚያም ነው አሁን በተቻለኝ አቅም በማደጎ ቤት ውስጥ ያሉ ልጆችን በቤቴ ሰብስቤ በገና ዋዜማ እራት የምጋብዛቸው'' ሲል ይናገራል።B





ለምን የልጅነት ጊዜውን ''አስከፊ'' ሲል ይገልፀዋል፡፡

ለምን ከማደጎ ቤት ከወጣ በኋላ ማንችስተር ከተማ በሚገኝ ማተሚያ ቤት ውስጥ የሥነ-ፅሑፍ ሥራውን እየሰራ ወላጅ እናቱን ማፈላለግ ጀመረ።

ወላጅ እናቱን ለበርካታ ዓመታት ካፈላለጋት በኋላ፤ 21 ዓመት ሲሆነው ጋምቢያ ውስጥ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እየሰራች የነበረችውን የማርእሸትን አገኛት።

ለምን ስለ ወላጅ እናቱ ሲናገር ''የእናቴ ፎቶግራፍ የተሰጠኝ ከተማረችበት ኮሌጅ ሲሆን፤ እናቴን ለመጀመሪያ ጊዜ ሳገኛት 21 ዓመቴ ነበር። ይህም እሷ አባቴን ያገኘችበት ዕድሜ ማለት ነው። እናቴ እና አባቴ ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኙት እኔ በተፀነስኩበት ምሽት ነበር።'' የሚለው ለምን ''የማርእሸት ሲሳይ አስደናቂ ሴት ናት። ካወራን የቆየንቢሆንም ብዙ ጊዜ ተገናኝተናል'' ሲል ያስታውሳል።

ዛሬ ላይ ለምን የበርካታ ተወዳጅ መጻህፍት፣ የተውኔት ድርሰቶች እና የግጥሞች ፀሃፊ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የማንችስተር ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ሲሆን ከሁለት የእንግሊዝ ሃገር ዩኒቨርሲቲዎች የክብር ዶክትሬቶችን ተቀብሏል።

ለምን እና ሥራዎቹ

ለምን ሲሳይ ''Gold from the stone''

ለምን ሲሳይ ስለ ስራዎቹ እና ስለ ግል ህይወቱ ለቢቢሲ አማርኛ ሲናገር ''ሁሌም ስለ እራሴ ታሪክ እና በማደጎ ቤቶች ውስጥ ያደረኩትን ትግልና ድል መጻፍ ያስደስተኛል። ያለፍኩበትን መንገድ ለሌሎች ማሳየት እፈልጋለሁ። መናገር የምፈልገውን ታሪክ ደግሞ በሥነ-ፅሁፍ መግለፅ ይቀለኛል።''

''በግጥም ማለት የማይቻለውን ሁሉ ማለት ይቻላል። ከልጅነቴ ጀምሮ ግጥም ትንቢታዊ ሃይል እንዳለው ይሰማኛል። በማደጎ ቤት ውስጥ እያለሁ የሚሰሙኝን የሃዘን ስሜቶች በግጥም ነበር የምገልፃቸው'' በማለት ለምን ለግጥም ያለውን ጥልቅ ስሜት ይናገራል።

"ለሥነ-ጽሑፍ ምን እንዳበረከትኩ አላውቅም። በሥነ-ጽሑፍ ሥራዎቼ ሰዎችን አነቃቅቼ ከሆነ ግን ትልቅ ኩራት ይሰማኛል።" ሲልም ተናግሯል፡፡

ለምን ከ15 ዓመት በፊት የፃፈው እጅግ የተወደደለት ''Something Dark'' የተባለው መጽሃፉ የህይወቱን ታሪክ የሚተርክ እንደሆነ ይናገራል። ''ይህንን መፅሃፍ ኢትዮጵያን ጨምሮ በተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት መድረክ ላይ አንብቤዋለው በቢቢሲ ሬዲዮም ተተርኳል'' ሲል ያስታውሳል።

ኢትዮጵያ እና ለምን

''እራሴን እንግሊዛዊ እና ኢትዮጵያዊ አድርጌ ነው የማስበው። ለኢትዮጵያ ጥልቅ ፍቅር አለኝ'' የሚለው ለምን፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ሥራዎቹን በተለያዩ መድረኮች እንዳቀረበ ይናገራል።

''ብዙ የሥነ-ጽሑፍ ስራዎቼ ወደ አማርኛ እንዲተረጎሙ ከኢትዮጵያውያን ጓደኞቼ ጋር እየተነጋገርኩ ነው። እዚህም በቅርብ የምጀመረው የነፃ የትምህርት እድል ፕሮግራም አለ። ይህ ፕሮግራም ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተማሪዎችን በተለየ መልኩ ተጠቃሚ ያደርጋል በዚህም ከፍተኛ ኩራት ይሰማኛል'' ይላል።

''በእንግሊዝ ሀገር ተወልጄ እንደማደጌ አማርኛ መናገር አልችልም'' አልችልም የሚለው ለምን ''Gold from the Stone'' የተባለው ሌላኛው መፅሃፉ በአሁን ጊዜ ወደ አማርኛ እየተተረጎመ እንደሆነ ተናግሯል።

ከሥነ-ጽሑፍ ሥራዎቹ በተጨማሪም ለምን በአሁን ወቅት የማንችስተር ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ሆኖ እየሰራ ይገኛል። ''እንደ ቻንስለርነቴ የዩኒቨርሲቲውን የቦርድ ስብሰባዎች እመራለሁ፤ እንዲሁም ተማሪዎችን አስመርቃለው። ቻንስለር ሆኜ ከተመረጥኩባቸው ምክንያቶች አንዱ የህግ ተማሪዎች ነፃ የትምህርት እድል እንዲያገኙ በማደርገው ሥራ ነው'' ይላል።

ለምን፤ አቢኢ [ኦርደር ኦፍ ዘ ብሪቲሽ ኢምፓዬር] የተሰኘው ክብር ተሰጥቶታል።

የማንችስተር ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር የሆነው ለምን በእንግሊዟ ዊጋን ከተማ በወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያ ነው ያደገው።

"ወጣቱ እኔ" በጭራሽ ይህን ክብር አገኛለሁ ብሎ አያስብም ይላል ለምን። ወጣቱ ለምን ሲሳይ ራሱን ለሥነ-ፅሑፍና ሰብዓዊ እርዳታ አሳልፎ የሰጠ እንደነበርም ያወሳል።

ከኢትዮጵያዊ እናት የተገኘው ገጣሚ ለምን ሲሳይ የብሪታኒያ መንግሥት በሙያቸው ብዙ ላበረከቱ ሰዎች የሚሰጠውን ክብር ከልዑል ቻርልስ እጅ ተቀብሏል።

ለምን የመጀመሪያውን የግጥም መድብሉን የ21 ዓመት ወጣት ሳለ ነው ያሳተመው።

'ማይ ኔም ኢዝ ዋይ' አሊያም በግርድፍ ትርጉሙ 'ስሜ ለምን ነው' በተሰኘው መፅሐፉ የብሪታኒያን የሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከላትን ታሪክ ልቅም አድርጎ ይተነትናል።

በፈረንጆቹ 1995 ኢንተርናል ፍላይት የተሰኘ ዘጋቢ ፊልም ከቢቢሲ ጋር በመጣመር ሠርቷል።

ሰምቲንግ ዳርክ የተሰኘው ብቻውን የሚተውንበት የራድዮ ቅንብርም በቢቢሲ ራድዮ 3 ጣቢያ ተላልፎለታል።

ለምን ኤም ቢ ኢ የተሰኘውን ክብር የተጎናፀፈው በፈረንጆቹ 2010 ነበር። ከማንችስተር ዩኒቨርሲቲ የቻንስለርነት ማዕረግ ያገኘው ደግሞ በ2015 ነው።

"እኔን ለመሰሉ በማሳደጊያ ማዕከላት ለሚገኙ ወጣቶች ይህን ማሳየት ትልቅ ነገር ነው። 'እኔም ይህን ላደርግ እችላለሁ' እንዲሉ ያደርጋቸዋልና" ይላል ለምን።

"እኚህ ወጣቶች 'እኔም ዶክተር መሆን እችላለሁ፣ አሊያም ጠበቃ፣ አሊያም ፀጉር አሳማሪ ወይም ደግሞ እሱ እንደሆነው እሆናለሁ' እንዲሉ ያስችላቸዋል።"

# የድሬዳዋ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

ጋር የተገናኘ በመሆኑ ተመራጭነቱን ያጎላዋል ብለዋል።

ነፃ የንግድ ቀጠናው በድሬዳዋ አስተዳደር ለሚገኙ ወጣቶች የስራ ዕድል በመፍጠር ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወትም ተናግረዋል። በመሆኑም አስተዳደሩ ነፃ የንግድ ቀጠናው የሚጠበቅበትን ግብ እንዲያሳካ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርግም ገልፀዋል።

በመድረኩ ላይ በነፃ የንግድ ቀጠና ጠቀሜታና ተግዳሮቶች እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ሚና በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፍ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠናን አስመልክቶ ለባለድርሻ አካላት ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ የፌደራልና የክልል ባለስልጣናት፤ ምሁራን፣ ባለሃብቶች ተሳትፈዋል፡፡

ለሶስት ቀናት በቆየው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አገር አቀፍ ውይይት ተጠናቆ የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ተጎብኝቷል፡ ፡ በጉብኝቱ ላይም የድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጣና በሙሉ አቅሙ ስራ ለመጀመርና የሎጅስቲክስና የንግድ ኢንቨስትመንቶችን ማስተናገድ የሚያስችል ቁመና ላይ እንደሚገኝ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ገብረመስቀል ጫላ ገልጸዋል።

ሚኒስትሩ የድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጣና ውስጥ የሚገኙና በተለያዩ የማምረቻው ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ሀገር በቀልና አለም አቀፍ ባለሀብቶች ያሉበትን የምርት እንቅስቃሴን ተመልክተዋል። በጉብኝቱ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ እና ሌሎች የኮርፖሬሽኑ አመራሮች ተገኝተዋል።

በዚህ ወቅት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ገብረመስቀል ጫላ ኮርፖሬሽኑ የድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጣናን በአጭር ግዜ ውጤታማ ለማድረግና በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ እንዲገባ ያከናወናቸዉ ስራዎች አበረታች መሆናቸውን አንስተዋል። አያይዘውም ነፃ ንግድ ቀጣናው በስራ እድል ፈጠራ፤ ተኪ ምርቶችን በማምረት፤ በቴክኖሎጂና በእውቀት ሽግግር የደረሰባቸው አበረታች ውጤቶች የሚደነቁ ናቸዉ ብለዋል።

ሚኒስትሩ አክለውም በቅርቡ በሙሉ አቅሙ ስራ እንዲጀምር በሎጀስቲክስ በንግድና በገቢና ወጪ ዙሪያ የተደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች ተጠናክረዉ መቀጠል እንዳለባቸው ገልጸው፤ ሰሞኑን እየተካሄደ የሚገኘው የባለድርሻ አካላት ውይይት ግብዓት እንደሚሆንም ጠቁመዋል።

የድሬዳዋ ነፃ ንግድ ቀጣና አሁን ላይ በማምረቻው ዘርፍ ባለሀብቶችን እያስተናገደ የሚገኝ ሲሆን በቅርቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ወደ ተወካዮች ምክር ቤት የተላከዉ የልዩ ኢኮኖሚክ ዞን አዋጅ ሲፀድቅ በንግድ፤ በሎጀስቲክስ፤ በገቢና ወጪ እንዲሁም በሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች ባለሀብቶችን መቀበል ይጀምራል።

# ዝክረ. . .

ከገጽ 1 የዞረ

ክቡር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራ በሙዚቃ ስራዎቹ ከፍተኛ እውቅናን እና አድናቆትን ከማትረፍም በላይ በተለያዩ ቋንቋዎች የተጫወታቸው ሙዚቃዎች ዘመን ተሻጋሪ እና ሁሌም የሚደመጡ ናቸው ። ክቡር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራ ጥቅምት 27/2015 ዓ.ም ህይወቱ ያለፈ ሲሆን የአርቲስቱን አንደኛ አመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግም በድሬዳዋ አስተዳደር ላይ ካሳለፍነው ሰኞ አንስቶ ለተከታታይ አምስት ቀናት በተለያዩ መርሀ-ግብሮች እንደሚከበር የድሬዳዋ አስተዳደር ክቡር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሀር ተናግረዋል ።

የክቡር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራ አንደኛ አመት መታሰቢያ መርሀ-ግብሮችም የጧፍ ማብራት ስነ-ስርአት ፣ የቢልቦርድ ምርቃት ፣ የፓናል ውይይት ፣ ስፖርታዊ ጨዋታዎች ፣ የኪነ-ጥበብ ዝግጅቶች ፣ በምድር ባቡር አደባባይ ላይ የሚዘጋጅ ኮንሰርት እንዲሁም በክቡር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራ ስም በተሰየመው ፓርክ ውስጥ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ይህ ጋዜጣ ለህትመት እስከተላከበት ድረስ እየተካሄደ ይገኛል ።

የአስተዳደሩ ክቡር ከንቲባ ከድር ጁሃር ለሚዲያ አካላት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ነዋሪው ህብረተሰብ በተዘጋጁት መርሀ-ግብሮች ላይ በመገኘት ለአርቲስቱ ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት እንዲገልፁ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

# የዋጋ ግሽበት

በበድሉ ሀይሌ

የዋጋ ግሽበትን ዘለቄታዊነት ያለውና በአብዛኞቹ ሸቀጣ ሸቀጦች ላይ የሚስተዋል የዋጋ ጭማሪ የሚል ብየና ልንሰጠው እንችላለን። የዋጋ ግሽበት ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገቡ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መካከል ዋነኛው ነው (የዋጋ ግሽበት በራሱ ምክንያትና ውጤት ስለሆነ)። በእርግጥ አሁን የሚስተዋለውን ኢትዮጵያን የዋጋ ግሽበት በተመለከተ ሙሉ ኢኮኖሚያዊ ትንታኔ መስጠት አዳጋች ነው። የዚህ ቁንፅል ጽሑፍ ዓላማ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ቅጥ ያጣ የዋጋ ግሽበት ምን ዓይነት የመፍትሔ ዕርምጃ ያሻዋል? ለሚለው ጥያቄ የራሴን ሐሳብ ለመስጠት ነው።

አሁን ያለው የኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት ከልክ በማለፉ ምክንያት፣ አብዛኛው ሕዝብ ምን ዓይነት ቤት ብገዛ ? ምን ዓይነት መኪና ብይዝ? የዕረፍት ጊዜዬን የት አገር (ቦታ) ሄጄ ባሳልፍ? ምን ዓይነት ትምህርት ብማር ይሻላል? የት ዩኒቨርሲቲ? ወዘተ ከሚሉት ጥያቄዎች በመውጣት፣ የቤተሰቦቼን ህልውና እንዴት ላሰንብት? (ምን ልብላ? ምን ልጠጣ? ልጆቼን እንዴት ላስተምር? ምን ልሥራ? የቤት ኪራይ እንዴት ልክፈል?...) ወደ ሚል ደረጃ ተሸጋግሯል።

እስከ እዚህ ድረስ ደርሷል የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ። አብዛኛውን ዜጋ የሚያገኘውን ገቢ ለመሠረታዊ ፍጆታ ወጪ ነው የሚያውለው። እርግጥ ነው ሕዝቡ አሁን ያለውን የዋጋ ግሽበት እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ የመታገስ አቅም ሊኖረው ይችላል (በባንክ የቆጠበውን እያወጣ፣ ሀብት ንብረቱን እየሸጠ፣ ከቻለም እየተበደረ በመጠቀም) ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ይህንን አቅም ሊያጣ ይችላል። ያ ደግሞ ወደ ሕገወጥነት፣ አለፍ ሲልም ወደ ‹‹የዳቦ አብዮት›› ሊያመራ ይችላል።

በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ በርከት ያሉ የዋጋ ግሽበት መነሾ ምክንያቶች አሉ ። ንድፈ ሐሳቦችን መመልከት ይቻላል)። ጠቅለል ማድረግ ከተቻለ ግን፣ በምርት እጥረት ሳቢያ የሚከሰት የዋጋ ግሽበት፣ በገንዘብ አቅርቦት ዕድገት ምክንያት የሚከሰት የዋጋ ግሽበትና ከውጭ የሚገባ የዋጋ ግሽበት በማለት መክፈል ይቻላል። ዞሮ ዞሮ የዋጋ ግሽበት መነሾዎች የተለያዩ ይሁኑ እንጂ መገለጫው ግን የምርቶች ዋጋ መናር ነው።

አሁን ካለው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ለዋጋ ግሽበት ዋና መነሾ መዋቅራዊ ተግዳሮቶች ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው መገመት አያስቸግርም። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በአሥር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በከፋ ድህነት ውስጥ ይኖራሉ የሚል ሪፖርቶች ወተዋል፡፡ ሚሊዮኖች በፀጥታ ችግር ከመኖሪያ ቦታቸው ተፈናቅለው የመንግሥትንና የህብረተሰቡን ቀጥተኛ ዕርዳታ ይሻሉ፡፡ ሚሊዮኖች በድርቅ ምክንያት ጥሪታቸውን አጥተዋል፡፡ ሚሊዮኖች ለዕለት የሚጎርሱት አጥተው የሰው እርጥባን ይሻሉ፡፡ ሚሊዮኖች ለሥራ አጥነት ተዳርገዋል፡፡

ሚሊዮኖች በፍርሃትና በሥጋት ውስጥ ሆነው ኑሯቸውን እየገፉ ይገኛሉ፡፡ በርካታ ፋብሪካዎች በፀጥታ ችግርና በምርት ግብዓት እጥረት ሳቢያ ተዘግተዋል ወይም ከአቅም በታች ያመርታሉ፡፡ መሠረተ ልማቶች በጦርነቱ ምክንያት ወድመዋል፡፡ ለአዳዲስ ጦርነቶች የሚጋብዙ ሁኔታዎች ከቀን ወደ ቀን እየሰፉ ናቸው፡፡ የግብርናው ዘርፍ በምርት ግብዓት ዋጋ ጭማሪ (መነሾው ዓለም አቀፋዊ ሊሆን ይችላል) እና በምርታማነት ማሽቆልቆል ምክንያት ችግር ውስጥ ገብቷል ወዘተ፡፡ እንዲህ ዓይነት ክስተቶች ባሉበት ሁኔታ የዋጋ ግሽበት እንዲረጋጋ መጠበቅ ሞኝነት ነው።

ከዚህ ጎን ለጎን ግን አንዳንድ ምርቶች አቅርቦታቸው ጥሩ ሆኖ እያለ ዋጋቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ እየመጣ ነው። ከዚህ በመነሳት ከመዋቅራዊ ችግሮች በተጨማሪ የገንዘብ አቅርቦት ዕድገት አሁን ላለው የኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት ሌላው መነሾ ሊሆን እንደሚችል መገመት ብልህነት ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ቀጥሎ ባለው ግጭት፣ አለመረጋጋት፣ ሥራ አጥነት፣ ድርቅና ረሃብ፣ መፈናቀልና የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት መቀዛቀዝ ጋር ተያይዞ የመንግሥት ገቢ (በተለይም ታክስ) ቀንሷል፣ ወይም ማደግ በሚገባው ልክ አላደገም።

ይህም መንግሥት የጀመራቸውን ፕሮጀክቶች ለማስቀጠልም ይሁን ሌሎች ክፍያዎችን ለመፈጸም የገንዘብ ህትመትን እንደ አንድ አማራጭ ሊወስድ ይችላል። ከዚህም ሌላ በተደጋጋሚ በሚዲያ እንደምንሰማው ጥቂት የማይባል የፎርጅድ ብር ኖቶች በኢኮኖሚው ውስጥ ይዘዋወራሉ።

በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው የዋጋ ግሽበት አብዛኛውን ዜጎች የጎዳውን ያህል፣ በዚያው ልክ ክስተቱን እንደ መልካም አጋጣሚ የሚቆጥሩት በርካቶች ናቸው። በተለይም ደግሞ በጅምላና በመካከለኛ ንግድ ተሰማርተው የሚገኙ ፈርጣማ ነጋዴዎችና በጥቅም የተሳሰሩ የመንግሥት አካላት በየሰዓቱ እየጨመረ የሚሄደው ዋጋ በርካታ ትርፍ እንዲያካብቱ ያግዛቸዋል። ይህም ደግሞ ዋጋ በሚፈለገው ልክ እንዳይረጋጋ እንቅፋት ይፈጥራል።

እንደ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበቱ ህብረተሰቡን በተለይም ቋሚ ገቢ ያላቸውን (ደመወዝተኞችንና የኪራይ ገቢ የሚያገኙትን) መፈታተኑ አይቀሬ ነው። የዋጋ ግሽበት ከሚያስከትላቸው ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መካከል ድህነት፣ የገቢ አለመመጣጠን፣ ሥራ አጥነት፣ የምርት መቀነስ፣ የጉልበት ብዝበዛና የሀብት ብክነት የሚሉት ይጠቀሳሉ። ይህም የዋጋ ግሽበትንና መዘዞችን ለማስወገድ መሠረታዊ የሚባሉ ዕርምጃዎችን መውሰድ ተገቢ እንደሆነ ያሳያል።

ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት በግሌ የሚከተሉት የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ ዕርምጃዎች ቢወሰዱ የዋጋ ግሽበቱን ለመቆጣጠር ያግዛል እላለሁ። ዕርምጃዎች በተለይም በምግብ ነክ ምርቶች ላይ የሚያተኮሩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አብዛኛውን የአገራችን የዋጋ ግሽበት ይበልጥ አሳሳቢ የሚያደርገው እንደ ምግብ ባሉ መሠረታዊ ምርቶች ላይ ይበልጥ የሚጎላ መሆኑ ነው።

**የአጭር ጊዜ ዕርምጃዎች፡-** የምግብ ነክ ምርቶች ላይ የሚስተዋለውን በአምራቹና በሸማቹ መካከል የሚገኙትን የአቅርቦት ሰንሰለቶችን ማጥበብ ብዙ ጊዜ በአምራቹና በተጠቃሚው መካከል ሌሎች ጥገኛ የሆኑ አካላት (ለምሳሌ ደላላ) ይገኛሉ። እነዚህ አካላት በምርት ላይ ከዚህ ግባ የሚባል እሴት ሳይጨምሩ፣ ነገር ግን በርከት ያለ ትርፍ በማጋበስ የምርት ዋጋ እንዲንር ምክንያት ይሆናሉ። ይህንን ችግር ለመቅረፍ በተለይም በግብርና ምርቶች ላይ የአምራቾችና የሸማቾች ማኅበራት ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት በቀጥታ እንዲተሳሰሩ በማድረግ፣ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸጡ ማድረግ ይቻላል።

ከዚህም በተጨማሪ እንደ ምግብ ዘይት የመሳሰሉ መሠረታዊ የፋብሪካ ምርቶችን አምራቾች ራሳቸው ለተጠቃሚዎች እንዲሸጡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የአቅርቦት ሰንሰለቱን መቀነስ ይቻላል። ለምሳሌ የምግብ ዘይት አምራች በዋና ዋና አካባቢዎች የሽያጭ ማዕከላትን በመክፈት፣ የዘይት ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ ለግለሰቦችና እንደ ሆቴል ለመሳሰሉ ድርጅቶች በቀጥታ መሸጥ ይችላል። በተመሳሳይ እንደ ዱቄት፣ ፓስታ፣ ማካሮኒ፣ ብስኩት፣ ስኳር፣ ቡና፣ ፍራፍሬዎችና እህሎች የተወሰነ ሥራ ከተሠራ አምራቾች ምርቶቻቸውን በቀጥታ ለተጠቃሚዎች የሚያደርሱበት ዕድል ሰፊ ነው።

**የምርት ክዘናን ፈፅሞ ማስወገድ፡-** የአንዳንድ ምርቶች በመጋዘን መከማቸት አቅርቦታቸው እንዲቅንስ፣ ብሎም የመሸጫ ዋጋቸው እንዲንር ያደርጋል። ይህንን በመረዳት ይመስላል በርካታ ነጋዴዎች የተለያዩ ምርቶችን በመከዘንና ሰው ሠራሽ እጥረት በመፍጠር በኋላ በውድ ዋጋ ሲሸጡ የሚስተዋለው። በመሆኑም መንግሥት ይህን ዓይነቱን ተግባር የሚፈጽሙ ነጋዴዎችን ተገቢውን አስተማሪ ዕርምጃ በመውሰድ መከላከል ይችላል። ይሁን እንጂ ይህን ዓይነት ሥራ የሚሠሩ አካላት በመንግሥት ሰዎችም ጭምር የሚደገፉ እንደሆኑ በተደጋጋሚ ይገለጻል።

**ድጎማ ማድረግ፡-** ለአምራቾች በተለይም ለአርሶ አደሮችና ለመሠረታዊ የፍጆታ ሸቀጣ ሸቀጥ አምራቾች የተለያዩ ማበረታቻዎችን በማድረግ፣ የምርት አቅርቦታቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ይቻላል። ይህም ሲባል የተለያዩ መሠረታዊ የምርት ግብዓቶች በመንግሥት በኩል ከገበያ ዋጋቸው ባነሰ ለአርሶ አደሮች እንዲቀርቡ በማድረግ የምርት አቅርቦት እንዲጨምር፣ ብሎም የመሸጫ ዋጋ እንዲቀንስ ማድረግ ይቻላል።

**ከውጭ የሚገቡ የቅንጦት ዕቃዎችን መቀነስ፡-** በግለሰብም ይሁን በመንግሥት በኩል በርካታ የውጭ ምንዛሪ ፈሰስ ተደርጎባቸው ከውጭ የሚገቡ፣ ነገር ግን ለኢኮኖሚው ምንም የማይፈይዱ (ወይም ብዙም አስተዋጽኦ የሌላቸው) የቅንጦት ምርቶችን በመቀነስ፣ ለምርቶች ግዥ የሚውለውን ምንዛሪ ለሌላ አስፈላጊ ዓላማ በማዋል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ብሎም የዋጋ ግሽበትን መቆጣጠር ይቻላል። በመንግሥት ደረጃ የሚመረቱ ምርቶችን አቅርቦት ማሳደግ እንደ ስኳር የመሳሰሉ በመንግሥት በኩል የሚመረቱ መሠረታዊ ምርቶችን አቅርቦት ማሳደግና በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ ማቅረብ፣ ዋጋን ለመቆጣጠር ይረዳል። የሸማቾችና የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማበረታታት ይገባል፡፡

**ከደመወዝ ጭማሪ ይልቅ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ፡-** ኢኮኖሚው ልክ እንዳሁኑ ሁለንተናው በተንኮታኮተበት ወቅት የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ፣ የደመወዝተኛውን ገቢ ከማሳደግ ይልቅ የዋጋ ግሽበቱን ይበልጥ ሊያባብሰው ይችላል። እርግጥ ነው በአሁኑ ጊዜ ሁሉም የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ እንዲጨመር ይፈልጋሉ፡፡ ይሁን እንጂ በመዋቅራዊ ችግሮች በተተበተበ ኢኮኖሚ፣ ይህ ዓይነቱ ዕርምጃ የብርን የመሸመት አቅም ከማኮስመን የዘለለ አይፈይድም። የደመወዝ ጭማሪ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ግን፣ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን ጨምሮ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን እስከማጠፍ የሚደርስ ዕርምጃን መውሰድ ሊጠይቅ ይችላል። ሌሎች ዕቅዶች ሳይነኩ የደመወዝ ክፍያን መጨመር ካስፈለገ ከሆነ፣ ምርታማነት በምን ያህል ተሻሽሏል? አድጓል? የሚለውን መመልከት ተገቢ ይሆናል።

ከላይ የተጠቀሱት ሐሳቦች የአጭር ጊዜ መፍትሔዎች ከመሆናቸውም ባሻገር፣ ከፍተኛ የመንግሥት ጣልቃ ገብነትን የሚሹ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ መንግሥት ለማስፈጸሚያነት ወጪ የሚደረገው ገንዘብ በተዘዋዋሪም ቢሆን በሕዝቡ የሚከፈል ነው። ለምሳሌ መንግሥት ለአርሶ አደሮች ድጎማ ሲያደርግ፣ ለድጎማ የሚወጣውን ወጪ የሚያካክሰው ከህብረተሰቡ ግብር በመሰብሰብ፣ የተለያዩ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎችንና ፕሮጀክቶችን በማጠፍ፣ እንዲሁም ገንዘብ በማተም ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ ከጊዜ በኋላ ከሌሎች ችግሮች በተጨማሪ ዋጋ ይበልጥ እንዲንር ሊያደርግ ይችላል።

## የረዥም ጊዜ ዕርምጃዎች

**የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤** የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በዋናነት በግብርናው ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን፣ ዘርፉን ማጠናከር ዋጋን ከማረጋጋት በዘለለ የሥራ ዕድልን በማስፋት፣ የውጭ ምንዛሪን ከማሳደግ፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት በመጨመር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ዘርፉን በመሠረታዊነት መለወጥ ያስፈልጋል።

**የመሬት ለምነትን በማሻሻል፣** የመስኖ ልማትን በመዘርጋት፣ እንደ ትራክተር፣ ኮምባይነርና የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎችን በመተግበር፣ የኩታ ገጠም እርሻን በመተግበር፣ የአካባቢ ጥበቃ ሥራን በማጠናከር የአፈር ለምነትንና የውኃ አቅርቦት ማሳደግ፣ የአርሶ አደሩን የቴክኖሎጂ አቀባበል ባህል በማጎልበት አብዛኛውን የግብርና ምርቶችን አቅርቦት በዘላቂነት ማሳደግ ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ ጥቅም ላይ ሳይውል የቀሩ መሬቶችን ለእርሻ እንዲውሉ በማድረግ፣ እንዲሁም በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚገኙ ዜጎች በአዋጭ የግብርና ዘርፎች እንዲሰማሩ በማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ ይቻላል። የግብርና ምርቶችናና ግብርና ነክ ጥሬ ዕቃዎች በብዛት ከተመረቱ የዋጋ ግሽበትን ትርጉም ባለው መንገድ መቆጣጠር ይቻላል።

**የወጪ ንግድን ማሳደግ፤** የወጪ ንግድን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ይቻላል። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ የተሻለ ጥቅም በምታገኝባቸው በቆዳ ውጤቶች፣ በጨርቃ ጨርቅ፣ በቅባት እህሎች፣ በቡናና በኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ወዘተ. ላይ ይበልጥ በመሥራትና ወደ ውጭ በመላክ በሚገኘው የውጭ ምንዛሪ የተሻሻሉ የማምረቻ ቴክኖሎጂዎችን በማስመጣት ምርትን ማሳደግ ይቻላል። ይህ ደግሞ የሥራ ዕድል ከመፍጠር፣ ለመንግሥት ገቢ ከማስገባት በተጨማሪ ዋጋን እንዲረጋጋ ያግዛል።

**ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ መተካት፤** በአገር ውስጥ መመረት የሚችሉ ምርቶችን በአገር ውስጥ ሀብቶች በማምረት መተካት ዋጋን በማረጋጋት ረገድ ጉልህ ፋይዳ ይኖረዋል። ከውጭ የሚገባ ምርት በአገር ውስጥ ሲመረት፣ የምርት አቅርቦት ከማሳደግና የውጭ ምንዛሪ ከማዳኑ በተጨማሪ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድልን ይፈጥራል። ከላይ የተጠቀሱትን ዕርምጃዎች መከተል፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እንዲሻሻል ስለሚያደርግ፣ የአገር ውስጥ ገንዘብ (ብር) የመግዛት አቅም እንዲሻሻል በማድረግ የዋጋ ግሽበት እንዲረጋጋ ያስችላል።

**ይቀጥላል . . .**


## ማስታወቂያ

የከዚራ ቶታል ነዳጅ ማደያ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ሮማን ብዙነህ ለድርጅቱ ስራ ሲጠቀሙበት የነበረው በግብር ከፋይ ቁጥር 0000711048 የሆነ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከ 20201 እስከ 34000 ምክኒያቱ ሳይታወቅ ጠፍቷል፡፡ ይህንን ደረሰኝ ወድቆ ያገኘ አሊያም ሌላ ሰው ሲጠቀምበት ያየ በቅርብ ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ እንዲያሳወቅ እየገለጽን ለሚያደርጉልን ቀና ትብብር እናመሰግናለን፡፡



## ማስታወቂያ

**ለአቶ አሊ ሙአሊን**

**ባሉበት**

አመልካች ወ/ሮ አያን አብደላ በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው በእርሶ ላይ እርሶ የሉም በማለት የፍቺ ክስ የተመሰረተቦት ስለሆነ እርሶ አልያም ይህን የፍቺ ክስ አቤቱታ ተቃዋሚ ካለ ለ17/03/2016 ዓ/ም ለሆነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ፤ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የፌ/መ/ደ/ሸ/ፍ/ቤት**


## “እንቅልፌን . . .

ከገጽ 3 የዞረ

በተጓዳኝ በመሰል የበጎ ፍቃድ ስራዎች ሲሰማራ ይህ የመጀመሪያው አለመሆኑን አስታውሰው ዘንድሮ ሰርቶ ካስረከባቸው ሁለቱ ቤቶች ውጭ ባለፉት አመታት ሁለት ተጨማሪ ቤቶችን ሰርቶ ማስረከቡን ገልፀዋል።

በቀጣይም ይህን በማጠናከር ይበልጥ ማህበረሰባችን በሚፈልግብን ሁሉ በመደገፍ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይን የበጎነት መርህ እናስቀጥላለን ነው ያሉት።

የወረዳ ሶስት ስራ አስኪያጅ ወ/ሮ ፀዳለ መካሻ በበኩላቸው ባለስልጣን መስሪያቤቱ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ለእናቶቹ ጥራት ያለው ቤት ገንብቶ በማስረከቡ አመስግነው መሰል የበጎ ፍቃድ ተግባራት ወረዳው በተለይ አቅመ ደካማ እናቶችን ለማገዝ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ አቅም ስለሚሆን በቀጣይም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

ቤት የተበረከተላቸው እናቶች ጎረቤቶችም መንግስት አሁን ላይ የከተማችን ሰላም እንዲጠበቅ ከማድረግ በዘለለ እንዲህ የተረሱ የተቸገሩ እናቶችን በመለየት መደገፉ እንዳስደሰታቸው እና ይህም በቀጣይ እንዲጠናከር ጥሪ አቅርበዋል።

**ምንጭ፡-የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን**

# የኛን ቁጠባ......በየኛ ውስጥ !

በኤደን ሳሙኤል

ማህበሩ ከ25 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል አክሲዮን በመሸጥ በተከፈለ 3 ሚሊዮን ብር ጅማሮውን አድርጓል፡፡ ከ370 በላይ አባላትንም ይዟል፡፡ ይህ የቁጠባና የብድር ማህበር "ከተረፈን ሳይሆን ካለን ላይ በመቆጠብ ለውጥ ማምጣት ይኖርብናል" ሚለውን መርህም ሰንቆ ነው የሚገሰግሰው የየኛ ቁጠባና ብድር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡ ሰላም ! ጤና ይስጥልኝ! ውድ የድሬ ጋዜጣ አንባቢያን እንዴት ከርማቹሀል? ሳምንታችሁ እንደተለመደው በመልካም እንዳለፈተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ውድ አንባቢያን ለዛሬ በቢዝነስ አምዳችን ስር ያዘጋጀሁላችሁ ፅሁፍ ከላይበመግቢያዬ ላይ ቆንጠር አድርጌ ላካፍላችሁ እንደሞከርኩት ስለ ቁጠባና ብድር ነው፡፡ በዋነኝነትም በቅርቡ በከተማችን ድሬዳዋ ተመስርቶ አሁን ላይ የብዙ የከተማችን ነዋሪዎችን ህይወት እያሻሻለ ስለሚገኘው ስለ የኛ ቁጠባና ብድር ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው የማወራችሁ፡፡ ለዚህም ደግሞ የማህበሩ ዋና ሊቀመንበር ከሆኑት ከአቶ ዳንኤል ታደሰ ጋር ቆይታን አድርጌአለሁ፡፡ እንዲሁም የማህበሩ አባል በመሆን ስራቸውን በማስፋፋት ተጠቃሚ ከሆኑ ነዋሪዎች ጋርም ቆይታን አድርጌ ለእናንተ ተሞክሮ የሚሆን ሀሳብን እና ልምድን አካፍላቹሀለሁ፡፡ መልካም ንባብም እንዲሆንላችሁ ተመኘሁ፡፡ አብራችሁኝ ዝለቁ፡፡

የኛ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር ሲመሰረት በዋነኝነት ሰው ካለው ላይ መቆጠብ አለበት የሚል መርህ በመያዝ ሲሆን ማንኛውም ሰው ቁጠባን መቆጠብ ያለበት ተርፎት ሳይሆን የኑሮውንና የገቢውን ሁኔታ በማጣጣም ካለው ላይ የተወሰነ ፐርሰንት በመደበኛነት የመቆጠብ ባህል ማዳበር አለበት ከሚል እሳቤ በመነሳት መሆኑን የማህበሩ አመራሮች ይናገራሉ፡፡ ኑሮአችንን ለመቀየርና በተሰማራንበት የስራ መስክምወደ ትርፍ የምንመጣው ስንቆጥብ ብቻ ነው ካልሆነናካልቆጠብን ግን ትርፍ ጋር መምጣት የህልም እንጀራ ነውም በማለት ሀሳባቸውን ያክላሉ፡፡ ቁጠባ ስር ነቀል ለውጥ እንደሚያመጣ በፅኑ እንደሚያምኑ የሚናገሩት ደግሞ የማህበሩ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ዳንኤል ታደሰ ናቸው፡፡

በየኛ ማህበር አሰራርም ቁጠባ ከተቆጠበ በኋላ ነው የብድር አገልግሎት ሰዎች የሚያገኙት በማለት ስለ ማህበሩ አሰራር የሚያብራሩት አቶ ዳንኤል ተቋሙከሌሎች የቁጠባ ተቋማትም ማለትም ከማይክሮ ፋይናንስም፣ ከባንክም ለየት የሚያደርገው አንድ ሰውብድር ለማግኘት መጀመሪያ አባል መሆን አለበት፣ ከዛም ሼሮችን መግዛት፣ ቀጥሎም የአባልነት መመዝገቢያ ክፍያን በመክፈል መመዝገብ ይጠበቅበታል፤ ይህንን ሂደት ጨርሶ ከተመዘገበና አባል ከሆነ በኋላወርሀዊ የግዴታ ቁጠባ የሚባል አለ እሱን መቆጠብ ይጀምራልበማለት የአባልነት ሂደቱን አቶ ዳንኤል ያብራራሉ፡፡

የወርሀዊ የግዴታ የቁጠባውም መጠን ከዝቅተኛው 300 መቶ ብር ጀምሮ አቅም እስከፈቀደ ድረስ መሄድ እንደሚቻልም ተናግረዋል፡፡ስለዚህ አንድ ሰው አባል ከሆነ ጀምሮ በቋሚነት የማህበሩ አባል መሆኑን ለማረጋገጥ ዝቅተኛ ቁጠባውን መቀጠል አለበት ያሉትአቶ ዳንኤል ይሄን ያደረግነውም የሰዎችን የቁጠባ ባህል ለማዳበር ነው በማለት ይናገራሉ፡፡ ማንኛውም አባል 300 ብሩን አባል እስከሆነ ድረስ በቋሚነት እየቆጠበ ይቀጥላልም፤ ይህም ግዴታ ነው ሲሉም አክለዋል፡፡

እንደ ሊቀመንበሩ ገለጻ የተቋሙ አባሎች አመታዊ የትርፍ ክፍፍልን የሚካፈሉ ሲሆን ለዚህ ደግሞ ዋነኛ መስፈርቱ ማለትም ትልቁን ቦታ የሚይዘው አባሉ ቁጠባውን በትክክል ቆጥቧል ወይ የሚለው ነው ብለዋል፡፡ በትክክል የቆጠበ አባልም ሼር ካለው ጋር በፐርሰንት ይቀመጥበታል ብለዋል አቶ ዳንኤል፡፡ የቁጠባ ፐርሰንትም አለው ስለዚህም በዚህ መሰረት አንድ ሰው ብድር ሲጠይቅም የጠየቀውን የገንዘብ መጠን ያህል ልክ የሚያገኘው በትክክል እየቆጠበ ነው ወይ የሚለው ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

ስለሆነም በየኛ ማህበር አሰራር ደንብ መሰረት አንድ ሰው ብድር ሲጠይቅብድር ስለጠየቀ ብቻ የፈለገውን አያገኝም በቅድሚያ የቁጠባ ባህሉን ማዳበር አለበትም ይላሉ ሊቀመንበሩ፡፡ባጠቃላይም ይሄ ማህበር የቁጠባ ባህልን ለማዳበር እንዲሁም አነስተኛ ኢኮኖሚ ያላቸው ሰዎች ላይ ሰፊ ስራን ለመስራት አልሞ የተቋቋመ የቁጠባና



የብድር ማህበር በመሆኑ ማንኛውም በአነስተኛ ብሎም በመካከለኛ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ለስራው ማስፋፊያ ብድር የሚሰጠው በቅድሚያ የቁጠባ ባህሉን ካዳበረ ብቻ መሆኑንሊቀመንበሩ አስረድተዋል፡፡

ማህበሩ እንዴት ተመሰረተ?

ማህበሩ የተመሰረተው በተለያዩ የስራ ዘርፎች ውስጥ የሚገኙ በእድሜያቸውም የተሰባጠሩ ማለትም ከተለያዩ ቢዝነስ ሴክተር የተውጣጡ የመንግስት ሰራተኛ ፣ በባንኩ ዘርፍ ያሉ ባለሞያዎች፣ ከንግዱ ማህበረሰብ እንዲሁም ደግሞ ከተቀጣሪውም የተቀላቀሉ ሰዎችን ይዞ መሆኑ ተነስቷል፡፡ በዚህም በመጀመሪያ ስለ ማህበሩ ምስረታ ሀሳቡን አንስተን ስንወያይ የነበርነው 10 አካባቢ ሰዎች ስንሆን ብዙ ከተመካከርንበት በኋላ ሀሳቡን ወደ መሬት ለማውረድም የመስራች ጉባኤያችንንየካቲት 22/2015 ዓ/ም ላይ ለማድረግ አቅደን ከዛም በእቅዱ መሰረት 40 የሚሆኑ ሰዎችን ይዘን የካቲት 22 የመስራች ጉባኤያችንን አካሄድን በማለት እለቷን አቶ ዳንኤል ያስታውሳሉ፡፡

ከዛም በአባል ቁጥር 985/2009 ማህበራትን ለማደራጀት በወጣው አዋጅ መሰረት እንደ ማህበር ለመመስረት ቢያንስ 50 ሰው መኖርአለበት ስለሚል አዋጁ ይሄንን ለሟሟላት ከማህበራት ማደራጃ አደራጅ ተመድቦልን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የግንኙነት አግባብ በመፍጠር እኛ በራሳችን የምናውቃቸውን ሰዎችንም የተቀላቀሉን ጥያቄ አቅርበን ሰዎችን በሟሟላት እንዲሁም ደግሞ የሚያስፈልገውን ዝቅተኛውን ካፒታል በመያዝ ወደ 77 አባላትን ይዘን በሚያዚያ 4/2015 ዓ.ምላይ ህጋዊ ሰርተፍኬት ማግኘት ችለናልም ሲሉ ሊቀመንበሩ ይናገራሉ፡፡

በኋላም የስራ ቦታችንን በአግባቡ አደራጅተን ለተወሰኑ ነዋሪዎችም የስራ እድልን በመፍጠር ወደ ስራ ገብተናል፡፡ በዚህም 5 ሰዎችን ቀጥረናል በማለት አቶ ዳንኤል ተናግረዋል፡፡ በመጀመሪያ ሰርተፍኬቱን ስንወስድ 77 አባላት ነበሩን አሁን ላይ ግን ከ370 በላይ አባላትን አፍርተናል ሲሉም አክለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኛ ተቋም ለየት የሚያደርገው የእቁብ ቁጠባ የሚል አለን ይህም ሙሉ ለሙሉ ዘመናዊ አሰራርን የተከተለ ነው ይላሉ፡፡

እቁብ እንደሚታወቀው በማህበረሰብ ውስጥ የተለመደ ባህላዊ የቁጠባ አይነት ሲሆን እኛም ይሄንን ባህል በመንተራስ የህብረተሰባችንን የቁጠባ ባህል አበረታተን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ በዘመናዊ መንገድ ተቋማዊ በሆነ መልኩ መተናል ፤ የእቁብ ቁጠባ እስካሁን በግለሰብ ደረጃ ነው ያለው፡፡ አሁን ላይ ግን በኛ ተቋም በማህበር መልክ አሳድገነዋልም ብለዋል ኃላፊው፡፡

በዚህም በመጀመሪያ የዚህ ዘመናዊ ዕቁብ አባል ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ አቅሙ በፈቀደው መጠንየገንዘቡን መጠን ወስኖ ምዝገባ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ከዛም ይቆጥባል እቁቡ ሲወጣለትም የሚወስድ ይሆናል በማለት ሊቀመንበሩ የእቁቡን ማለትም የዘመናዊ እቁቡን አካሄድ ያብራራሉ፡፡ እግረ መንገዳቸውንም ማንኛውም አባል በመሆን ቆጥቦ ህይወቱን መለወጥ የሚፈልግ አካል መጥቶ መመዝገብ ይችላል ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

በዚህ በዘመናዊ እቁብ ካሉት አዳዲስ ስርአቶች ውስጥ አንዱ ነገር ህጋዊነት ነው፡፡ በሀገራችን እንደሚታወቀው አብዛኞቹ እቁቦች ግለሰብ ላይ የተመሰረቱ እንዲሁም እምነትን የተንተራሱ እንጂ በህጋዊ መንገድ ውል የሌላቸው ናቸው፡፡በዚህ በየኛ ተቋም ግን የሚሰበሰቡ እቁቦች በሙሉ ህጋዊነታቸው የተረጋገጠና ውልን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ማንኛውም የዕቁቡ አካል በፈለገው ሰዓት ቢያቋርጥ፣ ቢወጣም፤ ቢገባምምንም አይነት ችግር የለውም፡፡ የዕቁቡ አባላትም ለቆጠቡበት ማለትም እቁቡን ለጣሉበት ህጋዊ ደረሰኝን ያገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሊቀመንበሩ ስለብድር አገልግሎት አሰጣጡ ሲናገሩ ብድሮቻችን ከ50 ሺ ብር ጀምሮ እስከ ተሽከርካሪ መግዣ፣ ቤት መገንቢያና እስከ 4 ሚሊየን ብር ድረስ የሚሄዱ ናቸው ይላሉ፡፡ በዚህም ማህበሩ ምስረታው አጭር ጊዜ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ከ 1.6 ሚሊዮን ብር በላይ ብድር እንደሰጠ አቶ ዳንኤል ተናግረዋል፡፡ 9 ለሚሆኑሰዎችም ብድርን ያበደሩ ሲሆን ይህም በተለያዩ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የድሬዳዋ ነዋሪዎች ነው፡፡የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑት ሰዎች ገንዘቡን ኢንቨስት ያደረጉበት የስራ ዘርፍም ማህበራዊ አስተዋጿቸውየጎላ ሲሆን እንደ ዳቦ ቤት፣ እንጀራ በመጋገርና በማከፋፈል ላይ ለተሰማሩ ሰዎች፣ ለሞባይል ቤት ላላቸው ፣ ት/ቤት ከፍተው ትውልድ ላይ እየሰሩ ለሚገኙና በእንዲህ አይነት ስራዎች ላይ ለተሰማሩ ሰዎች ብድሩ እንደተሰጠም ተጠቁሟል፡፡

እስካሁን ባለው ሁኔታም የአባላቶቻችን ካፒታልን በተመለከተ ወደ 25 ሚሊዮን ብር ሼር ለመግዛት የተመዘገቡ ሲሆን የተከፈለ ካፒታል ከ3 ሚሊዮን ብር በላይ ሰብስበናል በማለትም አቶ ዳንኤል ተናግረዋል፡፡ አሁን ላይ ደግሞ ለህብረተሰቡ ለማድረስ እየሰራንባቸው ያሉ አዳዲስ ስራዎች በስፋት አሉ ሲሉም አክለዋል፡፡ ታዲያ ከነዚህ አዳዲስ አሰራሮች መካከል አንዱከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት አንዱ ሲሆን በዚህ ዘርፍም 15 አባላቶች አሉን ብለዋል፡፡ አሁን ላይም በከፍተኛ ደረጃ ከወለድ ነፃ አገልግሎት ላይ የነዋሪዎች ፍላጎት ያለ በመሆኑ በዚህ ዙሪያ ያሉ አሰራሮችን አጠናክረን ብድሮችንም መስጠት እንጀምራለን ሲሉ ገልፀዋል፡፡

አሁን ደግሞ ውድ አንባቢያን የዚህ የየኛ ቁጠባና ብድር ማህበር አባል ሆነው ኑሮአቸውን ከለወጡ የከተማችን ነዋሪዎች ጋር ያደረግነውን ቆይታ ላካፍላችሁ፡፡ወ/ሮ ኩሪ ጉደታ የየኛ ብድርና ቁጠባ ማህበር አባል ናቸው፡፡ ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩትም እንጀራን ጋግረው በመሸጥ ነው፡፡ ወይዘሮዋ እንደሚገልጹት ከዚህ ቀደም በራሳቸው ጥረት የጀመሩትን የእንጀራ ንግድ ስራ በስፋት ለመስራትና ተጨማሪ ስራ ለመጀመር በማሰብ ከየኛ ቁጠባና ብድር ማህበር 50ሺ ብር እንደተበደሩ ይናገራሉ፡፡

ወ/ሮ ኩሪ በቀጣይም አሁን ባገኙት ገንዘብ ስራቸውን አጠናክረውና የተለያዩ የባልትና ውጤት ስራዎችን ጀምሮ ገቢያቸውን በማሳደግ ኑሮአቸውን መደጎም እንደሚፈልጉ አንስተዋል፡፡ አሁን ላይም በዚሁ ስራቸው 3 ልጆቻቸውን እያስተማሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ እንደኔም በየቤቱ ተደብቀው ያሉ ነገር ግን የመስራት አቅም ያላቸው ሴቶች ወደዚህ ተቋም ተቀላቅለው ቤተሰባቸውን እንዲያግዙ እመክራለሁ ይላሉ፡፡

"ያለመስራት ያስፈራል በተለይም በአሁኑ ጊዜ የኑሮ ውድነቱ ጣራ በነካበት ሰአት ሁሉም ወጪ በማይቀመስበት ጊዜ በቤተሰብ ደረጃ የሚኖሩ ሰዎች ማለትም ባለትዳሮች አንዱ ብቻ ሰርቶ ስለማይሆን አባወራን ብቻ ከመጠበቅ ይልቅ ሴቶችም ባላቸው ሞያ መስራት አለባቸው ስራቸውን ለማሳደግና ለማስፋፋት ደግሞ ወደነዚህ አይነት የቁጠባና የብድር ተቋማት መቀላቀላቸው ትርፉ የጎላ ነውም" ብለዋል ወ/ሮ ኩሪ፡፡ በተጨማሪም ወይዘሮዋ የቁጠባ ባህሌ አድጓል ለዚህም ማህበሩን ከልብ ማመስገን እወዳለሁ ይላሉ፡፡

ወ/ሮ ኩሪ ከዚህ ቀደም የነበራቸውን ህይወት ሲያስታውሱ እንዲህ ይላሉ፡፡ "እኔ በቀደመው ህይወቴ ስራን ባለመስራቴ ችግርተኛ ነበርኩኝ ልጆቼንም ወደ ት/ቤት ለመላክ እቸገር ነበረ፡፡ አሁን ላይ ግን በአቅሜ በቤቴ ውስጥ ስራን በመጀመር ለዚህ በቅቻለው በቤቴም ከጎሮቤቶቼ ጋር ተሰባስበን የምንጥለው እቁብም አለኝ፡፡ ብድርና ቁጠባዬንም በአግባቡ እየቆጠብኩ እገኛለሁ" ትላለች፡፡ በቀጣይም ደግሞ የፈጣሪ ፍቃድ ከሆነ ስራዬን በማስፋፋት ከደረቅ እንጀራ ጋግሮ ከመሸጥ ወደ በሰሉ ምግቦች ማለትም አነስተኛ ሆቴል ለመክፈት እቅድ አለኝ ትላለች፡፡

ሌላኛው የማህበሩ አባል የሆነው ወጣት በሪሁን ሰውአገኘሁ ሲባል በአሸዋ ሰፈር አካባቢ በሞባይል ሽያጭ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ ወጣት በሪሁን እንደሚለው በተበደረው ገንዘብ የሚሰራውን ስራ በማስፋፋት ስራው ላይ የገጠመውን የገንዘብ እጥረት እንደፈታለትና ማህበሩ የሚሰጠው አገልግሎት አላማዬን እንዳሳካ እረድቶኛል ሲልም ሀሳቡን ሰቶናል፡፡

"በህይወት ዘመኔ የተለያዩ ስራዎችን ሞክሬአለሁ በዚህም ሂደት ውስጥ በርካታ የሞከርኳቸው ስራዎች አሉ አዋጭነታቸውን አይቻለሁ፤ ግን ለማስፋፋት የገንዘብ እጥረት ስለገጠመኝ ተቻችኳለሁ" በማለት ወጣት በሪሁን በቁጭት ይናገራል፡፡ አሁን ላይ ግን ወደ የኛ ማህበር ተቀላቅዬ ብድር ከወሰድኩ አጭር ጊዜ ቢሆነኝምበትንሹ እየሰራሁት ባለው ስራ ላይ ማስፋፊያ አድርጌ ከ20 እስከ 30ሺ.ብር አትርፌአለሁ ይላል ወጣትበሪሁን፡፡

ስለሆነም ብድር ባላገኝ ኖሮ እንደ ከዚህ ቀደሞቹ በቁጭት ጊዜዬን ከማሳለፍ ውጪ ጠብ የሚል ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም እንደዚህ ውጤታማ አልሆንም ነበረም ሲልም ተናግሯል፡፡ "ቁጠባን ባህሌ አድርጌ በመበደሬ አትራፊ ሆኛለሁ ሌሎችም እንደኔ አይነት ወጣቶች ወደዚህ ተቋም መጥተው ስራቸውን እንዲያስፋፉ የቁጠባ ባህላቸውንም እንዲያጎለብቱ እመክራለሁም" ብሏል፡፡ ወጣት በሪሁን በሀሳቡ ማሳረጊያም የኛ ቁጠባና ብድር አክሲዮን ማህበርን ተመራጭ ያደረኩበት ዋነኛ ምክንያቴ ብርም ተበድሬ የሼርም ባለቤት ሆኜ ከማስገባው ወለዴም የሼር ክፍፍል ስለማገኝ ነው ሲል ይናገራል፡፡

በመጨረሻም ቁጠባ ላይ የሚሰሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በስፋት ሊሰሩ ይገባል ያሉት የማህበሩ ሊቀመንበር አቶ ዳንኤል አሁን ላይ በማህበረሰባችን ውስጥ ያለውን የስራ ባህል ለመቀየር የማማከር ስራዎችን በመስራት ውጤታማና ስኬታማ ማህበረሰብ ለመፍጠር አቅደን እየሰራን ነው ብለዋል፡፡

በመስተዳደሩ ከሚገኙ ሁሉም ማህበራት ጋርም በጋራ ተጋግዘን መስራት አለብንም ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ወጣቶችንም የዚህ ተቋም አባል በማድረግ ህይወታቸውን ማሻሻል ብሎም መቀየር እንዳለባቸው ስልጠናዎችን እንሰጣለን ያሉት አቶ ዳንኤልበተጨማሪም የማማከር አገልግሎትም በዚሁ በየኛ ማህበር ውስጥ እንደሚሰጥ ሊቀመንበሩ አንስተው የተለያዩ የቢዝነስ ሀሳቦችን በማቅረብም ለወጣቶች እገዛ እንደሚያደርጉም ገልጸዋል፡፡

## በፋይናንስ . . .

ከገጽ 1 የዞረ

አይነት መድረክ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የመንግስት ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ብለን ሐሰን በበኩላቸው ምዘናው በአቻ ተቋማት መካከል መከናወኑንና በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ለተቋሙ የተመደበው በጀት ለታቀደው ተግባር በተሻለ መልኩ ለሰሩ የመንግስት ተቋማት ተወዳድረው ሽልማቱ መከናወኑን ተናግረዋል፡፡

የመረጃው ምንጭ የአስተዳደሩ የገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ ነው፡፡

# ምንጩ

በትዕግስት ወልዴ

ከመንደራችን አንድ ፀጉረ ልውጥ ገና ሲደርስ “ማነው?”ብሎ መጠየቅ የተለመደ ባህላችን ነው፡፡ “ከየት መጣ?” እንላለን አይኖቻችን በጥያቄ ተሞልተው በጉጉት ተውጠን “ማነው? ”አንድም ቀን መጣ ከተባለው እንግዳ ሰው አዲስ ነገር ሰምቼ አላውቅም፡፡ በመንደራችን ካለው ከሀገሬው የተለየ ከሃሳባችን የራቀ ከህልማችን ያላበረ ከቅዠታችን ያልታሰረ ሰዲ ሰው አንድም ቀን ገጥሞኝ አያውቅም፡፡

ባለቤቱም ይለይ እንጂ ታሪኩ የእኛው ነው! ጉጉቴ እያደር ቀነሰ እንግዳ የለም!

አንድ ቀን ግን በማለዳ ከቤቴ ስወጣ አንድ ወጣት ለአይኔ እንግዳ የሆነ አየሁ! ትኩረቴን የሳበው መልከ መልካምነቱ አልነበረም፡፡ እንደ ደራሽ እንግዳ በአይኖቹ ጥርጣሬ አለማየቴ እንጂ! አይኖቹ ይስቃሉ ከንፈሮቹ ለአመል ሳይገለጡ፡፡

ያየሁት ከከተማው ከሚያስገባው አቅጣጫ ሲመጣ ነበርና እንደደረሰ ነው ስል አሰብሁ “ማነው?” በጭንቅላቴ ማሰብ የተውኩት ጥያቄ ብልጭ አለብኝ፡፡ ከዚያም ቀኑን በሙሉ የዛ ሰው ሁኔታ በሀሳቤ እየተመላለሰ ሳስብ ዋልኩ ፡፡

ቀትር ላይ ከምሰራበት ቦታ ተነስቼ ወደ ቤቴ ስሄድ ደግሞ ከፊት ለፊቴ መጣ ልንተላለፍ ጥቂት እንደቀረን ቆም አለ፡፡ እኔም እርምጃዬን ገታ አድርጌ አድክሞት ማረፊያ ፈልጎ እንደሆነ በማለት ወደ ቤቴ አብረን እንድንሄድ እና ምሳ እንድንበላ ጋበዝሁት አላመነታም፡፡

እንግዳን ማክበር የሀገራችን ወግ ነው ። “እንግዶች አምላክ ወደ ሰዎች የሚልካቸው አዲስ መልካም ነገር ይዘው ይመጣሉ ። “ የሚል የቆየ እምነት አለ፡፡

“የማይረባውንም እውቀት ወደ ሀገራችን ይዘው የሚመጡት እንግዶች ናቸውና ለአዳዲስ ሰዎች የተለየ ትኩረት መስጠት ጥሩ ነው ።” ይላሉ ፡፡

ለቤቴ ማማር ይሁን ከደጄ ከተከልሁት ትልቅ ሰፊ ዛፍ ጥላ የተነሳ ብዙ ጊዜ በእንግዶች እጎበኛለሁ ደጄሲንኳኳ ግባ ቤቴ ቤትህ ነው እላለሁ፡፡

የተለመዱትን ብቻ የሚያምኑት ጠንቃቃ ሰዎች ብዙ ጊዜ ይመክሩኛል፡፡

ሞትን አምኜ ከተወለድሁ ጀምሮ አብሬ ኖሬአለሁ፤ የእኔ ካልሁት ጠንካራ እና ደካማ ማንነት ለብዙ አመታት ኖሬአለሁ፤ ሰዎችን በፍቅር ከማመን በላይ የሚያስተሳስራቸው ምን አለና እላቸዋለሁ፡፡

ብዙ ጊዜ በሰፊው አዳራሽ ከተንጣለለው ጠረጴዛ የሚቀርበው የምግብ አይነት እና ብዛት ለገበታው የቀረበውን ሰው ብዛት የሚመጥን አይደለም፡፡ የተለመደውን ከአባትና እናቴ ቤት ስመለከት ያደግኩትን ባህል የተከተለ እንጂ የተትረፈረፈ ምግብ ማቅረብ የቤታችን ልማድ ነው፡፡

ለአይን የሚያጠግብ እንደሚሉት!

በጠረጴዛው ዙርያ ከእኔና እሱ ሌላ ሌሎች ሁለት የቅርብ ወዳጆቼ ነበሩ፡፡ አንድ የሆነ ነገር ሊነግረኝ እንደመጣ ሁሉ ልቤ እሱን ይጠብቃል ፡፡ ለወትሮው ብዙምለጨዋታ ችኩል አልነበርኩም፡፡ ልቤ በዚህ ሰው ተማርኮ ነው ልል ግን አልደፈርኩም ፡፡

ከብዙ የቃላት ጋጋታይልቅ እንደውህ ልብ ውስጥ ቀስ እያለ ጠብ የሚል ነገር እወዳለሁ፤ ቀስ እያለ የሚስማማ ። የምወደው አይነት ለዛ አለው ሲያወራ በየመሀሉ ያለው የዝምታ ግዜ እንደሙዚቃ የተመጠነ ነው ፡፡ አይጣደፍም!

የተዋበን ነገር የሚያስስ ዓይንና ጆሮ አለኝ የሚያምር ነገር እወዳለሁ፤ ለአይንም ለጆሮም ለልብም ፡፡

የሚያወጋው ስለመጣበት መንገድ ነው፡፡ ሙሉ ነገሩ ሲጀምር ያልነበርኩና ጨዋታው መሀል ድንገት የመጣሁ አይነት ስሜት እየተሰማኝ እና ቅር እያለኝ ሳዳምጠው ጓደኞቼ ግን በጨዋታው ተማርከው ፈዘውለታል፡፡

ከመጀመርያው ካልሰሙት እኮ ነገር አይጥምም፤ በወሬው መሀል ይሄን ተናገርሁ፡፡ ዞር ብሎ አይቶኝ ብዙ ትኩረት አልሰጠኝም መሰል ካቆመበት ወሬውን ቀጠለ፡፡

ሰውየው ምነው እንዲህ ያምራል? ከላይ እስከታች ያማረ ግርማ ሞገሳም ነው የድምፁ መጎርነን ልቤን ሊንደው እንደሚታገል ኃይለኛ ወራጅ ይነቀንቀኛል፡፡

ለአመታት ልቤንለወንድ ሰጥቼ አላውቅም፡፡ ወንዶችን እንደጓደኛ ስለምቀርብፍቅረኝነት ከጓደኝነት እየተቀላቀለብኝ ብዙ ግዜ እቸገራለሁ፤ አፈቀርኩት እልና ፍቅሩ አልዘልቅ ይለኛል፡፡

ይህ አመጣጡ ለምን እንደሆነ ያላወቅሁት እንግዳ ሰው ግን እንዲሁ አካሄዱ ሁሉ የተጠና ነገር ይመስላል የሆነ ደስ የሚል ስሜት ቢፈጥርብኝም ላምነው ግን አልቻልኩም፡፡

መንገዱ ረጅም ነው መሰለኝ ? አልኩት አፌ ለምን ዝም ሊል እንዳልቻለ እግዚአብሔር ይወቅ እሱም ምንም እንዳላልኩ ዞር እንደማለት ብሎ ካቆመበት ወሬውንቀጠለ ። ልቤ ቅሬታ ገባ !

ወሬውን ለመቋጨት “ይኸው በመጨረሻ እዚህ ቤት ደረስኩ !” አለ፡፡ ጓደኞቼ ሳቅ አሉ ። ወደ እኔ ዞሮ ምን ነበር ያልሽኝ ሲል ጠየቀ በእርግጥ የፈለግሁት ታሪኩን ከቤቱ ቢጀምርልኝ ነበር፡፡ ከመጣበት አላማ ጋር ጨዋታው ቢነገረኝ እፈልግ ነበር፡፡ የት ሊሄድም በዚህ እንደሚያልፍ ልሰማ ፈልጌአለሁ ፡ ፡ ያንን ፍላጎቴን ግን ለማሳየት ስላልፈለግሁ ዝም አልኩት ነገሩን ባውቀውስ ምን ሊጨምርልኝ ስል በልቤ ተፅናናሁ፡፡ ምሳችንን በልተን እስክንጨርስ ዝም እንደተባባልን ቆየን ለመሄድ ሲነሳ ለረጅም ግዜ እንደሚተዋወቅ ወዳጅ ትከሻዬን ያዝ አድርጎ በቤቴ ስለነበረው ጊዜ አመሰገነኝ ፡፡

በሰላም ግባ ! አልኩት የጉጉቴን ያህል ምንም ልሰማበት አለመቻሌ እየገረመኝ መልሶ እንዲመጣ እንዳልመኘም ንቀቱ እልህ አስያዘኝ መሰል የሚቀጥል ወዳጅነት እንዲኖረን እንኳን ባለመፈለግ ደና ሁን ብዬ ተሰናበትኩት ። ከሄደበት ቀን በኋላም ፈፅሞ ትውስ አላለኝም፡፡

ከወራት በኋላ ከዛ ሰው አንድ ደብዳቤ ደረሰኝ፡- “እንደምን ከርመሻል ? መቼምእኛ ሀገር ስላለው የምንጭ ውሀ አፈታሪክ ሳትሰሚ አትቀሪም ምናልባት ያንን ቦታ የማየት ጉጉት አድሮብሽ እንደሆን ስትመጪ እኔ ቤት ምሳ ተጋብዘሻል፡፡”

የሚል ነበር ከቤቱ አድራሻ ጋር የተላከልኝ ከየትኛው ሀገር እንደመጣም ከጨዋታው ተረድቼ ነበር ፡፡ በልጅነቴ ከአባቴ ጋር ወደዚያ መሄዴ ትውስ ይለኛል፡፡

‘እዛኛው ሀገር ያለው የምንጭ ውሀ አፈታሪክ ምንድነው ?’ ከጓደኞቼ ጋር ተሰብስበን ስናወራ ጠየቅሁ ከጓደኞቼ መሀል ማናቸውም ስለዚህ ምንጭ አያውቁም ማታ ወደ መኝታዬ ከመሄዴ በፊት በቤት ካሉት አገልጋዮች በእድሜ የበሰሉትን ያ ሰው ስላቀረበኝ ግብዣ አወራኋቸው፡፡ እሳቸውም እንዲሁ አሉኝ ፡- “በእርግጥ ሀገሩ እርጥብ ነው ብዙ ምንጮችም ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ አባቶቻችን ሲያወሩ እንደሰማሁት ከሆነ ግን ስለአንድ ምንጭ ታሪክ አውቃለሁ፡፡ ያ ምንጭ እዚህ ቅርብ ያለ ሳይሆን ምናልባት በሌላኛው አለም የሚገኝ ነው ሲሉ ነው የሰማሁት፡፡”

እስቲ ይንገሩኝ?

“ድሮ የሰው ልጆች ሁሉ አባት የሆነውን አዳምን ፈጣሪ በአንዲት ምንጭ ዳርቻ ነበር አፈሩን ዘግኖ ከዛ ምንጭ ውሃ ጨልፎ ያበጀው ታዲያ አባታችን አዳም ከተፈጠረበት እለት ጀምሮ ከዛች ምንጭ ውሀ በፍቅር ወድቆ እዛው ይተኛ ነበር፡ ፡ ይሄንን ያየው ፈጣሪም አንድ ቀን በሌሊት አጋሩን አበጀለት፡፡

ለመጀመርያጊዜ በዛ ማለዳ የፍጥረት ቀኗ ብስራት እንደታወጀ ፊቷን በዛ የምንጭ ውሃ ነፀብራቅ ተመለከተች እጅግ ውብ ነበረችናከምንጭ ውሀው ባየችው ምስሏ እጅግ ተማርካ እንደፈዘዘች የሰው ልጆች አባት የሆነው አዳም አገኛት ለመጀመርያ ጊዜ የተያዩትም ፊት ለፊት ሳይሆን በዚያ እንደመስታወት በሚያንፀባርቀውእና ኩልል ባለው የምንጭ ውሀ ነበር ፡፡”

ታሪኩን በመገረም ነበር የሰማሁት ልቤ በጉጉት ተሞላ፡፡ ‘ይሄ ምንጭ እዛ ሰው ሀገር ይኖር ይሆን?’ ብዬም ጠየቅኋቸው፡፡

“አይመስለኝም! ይሄ የሆነው ጥንት እና እጅግ የራቀ ሀገር ነው ።” አሉ፡፡ ከዛ ወዲያ ሴትየዋን አልሰማኋቸውም አካሌ እዛው ቆሞ ልቤ እዛ ሰው ሀገር ገባ፡፡

“ምናልባት” አሉኝ እኚህ ብልህ ሴት ቀልቤ እስኪመለስ አይን አይኔን እያዩ “ይሄ ጥበበኛ ሰው ሳይሆን አይቀርም እና ምላሽ ሳትሰጪ ትንሽ ጠብቂው፡፡” አሉኝ “ወደ የትኛው አቅጣጫ ሊወስድሽ እንደፈለገ ሳትረጂ አንድም እርምጃ እንዳትሄጂ፡፡” ከሰውየው ግብዣ ሴትየዋ የተረዱት ምን እንደሆነ ያኔ ነው የገባኝ፡፡

ግን..........! አልኳቸው በማመንታት ሄጄ ነገሩን ባይስ? ሁለታችንም ሴቶች ነን እና ልቤ እንደከጀለው ወድያው ስለገባቸው በዓይናቸው ገረፍ አደረጉኝ፡፡

“ይኸውልሽ ያ ቀን እኮ ለሴቲቱ የፍጥረት ቀኗ እንደነበር ለአዳምም የመጉደል ቀን ነበር በእርግጥ ነገሩ እሱ እንደሚለው ከሆነ መምጣቱ አይቀርም እና እዚህ ተቀምጠሽ ጠብቂው፡፡” አሉኝ፡፡

## የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ ማርያም ሰፈር 1ኛ እና አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የግዥ/ፋ/ን/አስ/ደ/የስራ ሂደት በ2016 ዓ.ም የበጀት ዓመት

ሎት 1.ለቢሮ አላቂ ዕቃዎች

ሎት 2..ለትምህርት አላቂ ዕቃዎች

- የስፖርት ትጥቆች
- የኤሌክትሪክ ዕቃዎች
- የቧንቧ እቃዎች

ሎት 3. ለፅዳት አላቂ ዕቃዎች

ስለዚህ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1. የመስኩ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው የዘመኑን ግብር የከፈሉ
2. የ VAT ተመዝጋቢ የሆኑ TIN No ያላቸው ከገቢዎች ባለሥልጣን ተመዝጋቢ መሆናቸውን ማቅረብ የሚችሉ
3. ተጫራቾች የቀረበውን የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታ ሰነዱን በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ሰዓት በት/ቤቱ ቢሮ ቁጥር R-2 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዳቸውን ኦርጅናልና የሚነበብ ኮፒ ለየብቻ በመግለጽ በሰም በታሸገ ኤንቬሎፕ በማድረግ የጨረታ ማስከበሪያ ብር

   ለሎት አንድ 5000 ብር

   ለሎት ሁለት 5000 ብር

   ለሎት ሦስት 5000 ብር

   በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም (CPO) ከጨረታ ሰነድ ጋር በማያያዝ በት/ቤት በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉ 15 ቀናት ውስጥ ክፍት ሆኖ ከቆየ በኃላ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡00 ሰአት ታሽጎ 3፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በማርያም ሰፈር 1ኛ እና አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ቢሮ ቁጥር R-3 ይከፈታል፡፡ ይህ ቀን እሁድ እንዲሁም የበዓል ቀን ከሆነ ቀጣይ የስራ ቀን በዚሁ ተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች ግዥን ማሸነፋቸው ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ት/ቤቱ ድረስ በመምጣት ዕቃውን ማስረከብ አለባቸው፡፡
7. ት/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው
8. የሚቀርቡ እቃዎች የኢትዮጵያን ጥራት ደረጃዎች ኤጀንሲ ስታንዳርድ ባወጣው ዝርዝር መሰረት መሆን አለበት፡፡

ማሳሰቢያ፡-

- ማናቸውም ተጫራቾች ዋጋውንም በዚህ ዶክመንት ላይ ሞልቶ ማህተም አድርጎ ሙሉ ሰነድ መመለስ አለበት፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡- በስ/ቁ 025 -111 13 32 ሞባይል 09 13 68 30 02 ይደውሉ**

## ማስታወቂያ

**ለአቶ ሮዚ አባስ**

**ባሉበት**

አመልካች ወ/ሮ ሀጀራ ነጅብ በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው በእርሶ ላይ እርሶ የሉም በማለት የፍቺ ክስ የተመሰረተቦት ስለሆነ እርሶ አልያም ይህን የፍቺ ክስ አቤቱታ ተቃዋሚ ካለ ለ11/03/2016 ዓ/ም ለሆነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ፤ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የፌ/መ/ደ/ሸ/ፍ/ቤት**

## ማስታወቂያ

የአብዱረዛቅ መሀመድ ጠቅላላ አስመጪና ችርቻሮ ንግድ ሥራ አስኪያጅ አቶ አብዱረዛቅ መሀመድ ለድርጅቱ ስራ ሲጠቀሙበት የነበረው በግብር ከፋይ ቁጥር 0058805116 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከ0000 እስከ 0100ምክኒያቱ ሳይታወቅ ጠፍቷል፡፡ ይህንን ደረሰኝ ወድቆ ያገኘ በ09 15 73 39 41 ሞባይል ቁጥር ደውለው እንዲያሳውቁ፤ አሊያም ሌላ ሰው ሲጠቀምበት ያየ በቅርብ ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ እንዲያሳወቅ እየገለጽን ለሚያደርጉልን ቀና ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ የመኪና ጥገና ጨረታ ማስታወቂያ

ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ግዥ ክፍል ቁጥር 3 በመውሰድ የመወዳደሪያ ዋጋ የያዘውን ሰነድ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ በማድረግ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከ15 ቀናት በኃላ (በ16ኛውቀን) ከጠዋቱ 3፡30 ድረስ ለዚህ ተግባር በተዘጋጀውና በግዥ፣ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ውስጥ በሚገኘው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

በጨረታው ለመሳተፍ፡-

- የዘመኑን ግብር የተከፈለበት የታደሰ የንግድ ፍቃድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ተመዝጋቢ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናገንዘብ/ ቢን ቦርድ በ4 ባንክ የተመሰከረለት የክፍያ ትእዛዝ CPO ከሚወዳደሩበት ጠቅላላዋጋ ብር 5000.00 ማቅረብ የሚችሉ፣
- አንድ ተጫራች በሚያቀርበው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ መቀነስም ሆነ መጨመር የማይችል መሆኑን፡፡
- የጨረታ ሳጥኑ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከ15 ቀናት በኋላ (በ16ኛውቀን) ከጠዋቱ በ3፡30 ይታሸጋል፡፡
- ጨረታው በ16ኛ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመ/ቤቱ አዳራሽ የሚከፈት መሆኑን፡-
- መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ወይም መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ስለጨረታው ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ በስ/ቁጥሮች0993-67-21-57/09-29-25-04-71ደውሎ መጠየቅ የሚቻል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ**

## Invitation to Bid Notice (LCB)

1, To: ALL CONTRACTORS OF GC/BC-9 & 8 CONSTRUCTION ENTERPRISES WITH LICENSE VALID FOR THE YEAR 2016

2, the D.D Administration Health Bureau has fund with procurement entity budget to be used for the procurement of for construction of Health Facility Renovation Located at Legeoda gudufeta Health Center

3, all eligible bidders should present from the mandated public body:

- Renewed trade license for the year
- Supplier certificate in Dire Dawa Administration
- Renewed professional certificate of registration
- Tax clearance and VAT registration certificate
- Micro and Small enterprise certificate & level of grade from the Administration Micro and Small enterprise Development agency.

4, A complete set of bidding document may be purchased by any interested eligible bidder on the submission of a written application to the D.D Administration Health Bureau Room No __ up to payment of 200(two hundred BIRR ONLY)

5, Bidding will be, conducted in accordance with open national tendering procedures contained in the public procurement proclamation of the Federal Gov't of Ethiopia and is open to all bidders from eligible source countries.

6, interested eligible bidders may obtain further information from D.D Administration Health Bureau and inspect the bidding document at the address given below from 7:30- 12:00Am & 2:00-5:30 pm working hours.

7, Bids must be delivered to the address below at or before 9: 00A.M on the 15th Date from the date of Announcement. Bids shall be valid for a period of 90 days after bid opening and all bids must be accompanied by a bid security 5,000(five thousand birr) in the form of cash, a certified check or payable order, bank draft, letter of credit, or an unconditional bank guarantee. The bid security shall be valid for 28 days beyond the validity of the bid. Late bids shall be rejected.

8, Bids will be opened in the presence of bidders representatives who choose to attend at the same place & Date at 9:30AM at the office of D.D Administration Health Bureau

9, The Construction works shall be complete within a maximum 120 calendar days from the commencement of the work.

10, The Employer Reserves The Right to Reject Any or All Bids

**Address: D.D Administration Health Bureau**

**Telephone No. 025-1-11-23-30 e-mail address ddhealth@ethionet.et**

**Post No. 1377 Fax 025-1-11-42-5**

## Invitation to Bid Notice (LCB)

1, To: ALL CONTRACTORS OF GC/BC-9 & 8 CONSTRUCTION ENTERPRISES WITH LICENSE VALID FOR THE YEAR 2016

2, the D.D Administration Health Bureau has fund with procurement entity budget to be used for the procurement of for construction of STAFF RESIDENCE BLOCK Located at Biyo Awale Health Center

3, all eligible bidders should present from the mandated public body:

- Renewed trade license for the year
- Supplier certificate in Dire Dawa Administration
- Renewed professional certificate of registration
- Tax clearance and VAT registration certificate
- Micro and Small enterprise certificate & level of grade from the Administration Micro and Small enterprise Development agency.

4, A complete set of bidding document may be purchased by any interested eligible bidder on the submission of a written application to the D.D Administration Health Bureau Room No __ up to payment of 200 (two hundred BIRR ONLY)

5, Bidding will be, conducted in accordance with open national tendering procedures contained in the public procurement proclamation of the Federal Gov't of Ethiopia and is open to all bidders from eligible source countries.

6, interested eligible bidders may obtain further information from D.D Administration Health Bureau and inspect the bidding document at the address given below from 7:30- 12:00Am & 2:00-5:30 pm working hours.

7, Bids must be delivered to the address below at or before 9: 00A.M on the 15th Date from the date of Announcement. Bids shall be valid for a period of 90 days after bid opening and all bids must be accompanied by a bid security 5,000(five thousand birr) in the form of cash, a certified check or payable order, bank draft, letter of credit, or an unconditional bank guarantee. The bid security shall be valid for 28 days beyond the validity of the bid. Late bids shall be rejected.

8, Bids will be opened in the presence of bidders representatives who choose to attend at the same place & Date at 9:30AM at the office of D.D Administration Health Bureau

9, The Construction works shall be complete within a maximum 120 calendar days from the commencement of the work.

10, The Employer Reserves The Right to Reject Any or All Bids

**Address: D.D Administration Health Bureau**

**Telephone No. 025-1-11-23-30 e-mail address ddhealth@ethionet.et**

**Post No. 1377 Fax 025-1-11-42-5**

## ማስታወቂያ

**ለአቶ አህመድ መሀመድ**

**ባሉበት**

አመልካች ወ/ሮ ሀያት አብዱረሀማን በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው በእርሶ ላይ እርሶ የሉም በማለት የፍቺ ክስ የተመሰረተቦት ስለሆነ እርሶ አልያም ይህን የፍቺ ክስ አቤቱታ ተቃዋሚ ካለ ለ10/03/2016 ዓ/ም ለሆነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ፤ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የፌ/መ/ደ/ሸ/ፍ/ቤት**

## ማስታወቂያ

**ለአቶ አህመድ ሣኒ**

**ባሉበት**

አመልካች ወ/ሮ ኑሪያ አብዱላሂ በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው በእርሶ ላይ እርሶ የሉም በማለት የፍቺ ክስ የተመሰረተቦት ስለሆነ እርሶ አልያም ይህን የፍቺ ክስ አቤቱታ ተቃዋሚ ካለ ለ29/02/2016 ዓ/ም ለሆነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ፤ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የፌ/መ/ደ/ሸ/ፍ/ቤት**

## ማስታወቂያ

**ለአቶ አብዱረሀማን ኡስማኤል**

**ባሉበት**

አመልካች ወ/ሮ ሮውዳ አዲስ በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው በእርሶ ላይ እርሶ የሉም በማለት የፍቺ ክስ የተመሰረተቦት ስለሆነ እርሶ አልያም ይህን የፍቺ ክስ አቤቱታ ተቃዋሚ ካለ ለ29/02/2016 ዓ/ም ለሆነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ፤ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ያሳውቃል፡፡

**የፌ/መ/ደ/ሸ/ፍ/ቤት**

## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ አስተዳደር የድልጮራ ሆስፒታል ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘዉን ካፍቴሪያበግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት እና ለማከራየት ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት በጨረታው ላይ ለመካፈል የሚፈልጉ ተጫራቾች፡፡

1. በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ መሆን ይኖርባቸዋል፤
2. ተጫራቾች በዘርፉ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸውና የ2016 ዓ/ም ግብር የከፈሉ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው ፡፡
3. በመንግስት ግዥ አቅራቢ የሆኑ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የታክስ መለያ ቁጥር (Tin no) ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቅያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት ለ15 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 300.00 (ሶስት መቶ) እያንዳንዱ ሎት በመክፈል በድልጮራ ሆስፒታል ቢሮ ቁጥር A\02 በማቅረብ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
6. መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበርያ የሚሆን ብር 10,000.00 (አስር ሺ ብር) በባንክ በተመሰከረለት ቼክ ወይም (CPO) ከጨረታው ኦርጅናል ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለዚህ ብሎ በተዘጋጀው የጨረታ መቀበያ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል ፡፡
8. የጨረታ ሰነዱ የሚከፈትበት ቀን ይህ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 የስራ ቀናት ከቆየ በኃላ በ16ኛው ቀን ጠዋት 4፡00 ሠዓት ተዘግቶ ከቀኑ 4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሆስፒታሉ ግዥ ፋ/ን/አስዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር A\02 ይከፈታል፡፡
9. የጨረታው አሸናፊ አሸናፊነቱ በፅሁፍ እንደተገለፀለት አስፈላጊውን የጨረታ ውል ማስከበሪያ 10% በማስያዝ ከሆስፒታሉ ጋር ውል መፈራረም ይኖርበታል፡፡ ይህ ባይፈፀም አሸናፊነቱ ተሰርዞ ለጨረታ ማስከበርያ ያስያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይሆናል ፡፡
10. ተጫራቾች በሰነዳቸው ላይ ስማቸውን ሙሉ አድራሻቸውን እና ፊርማቸውን እንዲሁም የተሟላ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
11. ሆስፒታሉ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- በድሬዳዋ አስተዳደር የድል ጮራ ሆስፒታል**

**ስልክ ቁጥር 0982540408//02-521115693፡ ፖስታ ሳጥን ቁጥር 177**

## የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ ከተማ የ06 ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በስሩ ለሚገኘው ለሀዳሴ 1ኛ ደረጃ ት/ቤትለ2016 በጀት አመት የተለያዩ የጽህፈት መሳሪያና የጽዳት እቃ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎችና መጽሐፍት በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ተጫራቾች ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሰው መስፈርት መሰረት፡፡-

1. ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያለው
2. በአቅራቢነት የተመዘገበ
3. የዘመኑን ግብር የከፈለ
4. ቫት የከፈሉ እና የተመዘገበበትን የሚያቀርብ
5. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 3000.00 /ሦስት ሺህ ብር/ በቀበሌ 06 ስም በተዘጋጀው በባንክ የተረጋገጠ (Cpo ) ወይም በጥሬ ገንዘብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. በጨረታ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 250.00/ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ ፡፡
7. ተጫራቾች የዋጋ ዝርዝራቸውን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ዋናውንና ኮፒውን 2ቱንም ይህ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 /ተከታታይቀናትየፋ/ ግ/ ን/ አስተዳደር ቢሮ ቁጥር 006 በመምጣት ባዘጋጀነው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ ፡፡
8. ጨረታው የሚከፈተው በ6/ 3 / 2016 ዓ.ም ሲሆን ከጠዋቱ 3፡30 ታሽጎ 4 ሰዓት ላይ የፋይ/ ግዢ/ንብ/ አስ/ ሂደት ቢሮ ቁጥር 006 የሚከፈት መሆኑን እንገልፃለን ፡፡

ማሳሰቢያ ፡-

1. ጨረታው በሚከፈትበት ወቅት የድርጅቱ ባለቤት ወይም ህጋዊ ተወካይ መገኘት ይኖርበታል ፡፡
2. መስሪያ ቤቱ ጨረታውን በከፊልምወይምበሙሉ የመሰረዝመብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
3. ተጫራቾች በጨረታው መክፈቻ ቀን ምንም አይነት ጨረታ ሸያጭ ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም ፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ ሲመልሱ የሚያስገቡትን እቃ ዓይነት / ሳምፕል አብረው እንዲያስገቡ እናሳስባለን፡፡

ለበለጠ መረጃ፡-

በስልክ ቁጥር 0251 12 34 59 ሞባይል 09-15-76-74-66 ወይም 09-15-76-28-88 በመደወል ወይም ቀበሌ 06 ፋ/ግ/ን/አስ/ደ/የስ/ሂደት ቢሮ ቁጥር 006በአካል በመሄድ ይጠይቁ፡፡

## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በመልካ ጀብዱ ጤና ጣቢያ የ2016 በጀት ዓመት የእስቴሽነሪ እና የጽዳት እቃዎች በድሬ ጋዜጣ ላይ በድጋሚ የጨረታ ማስታወቂያ አውጥተናል፡፡ ስለሆነም ተጫራቾች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ሎት 1. እስቴሽነሪ

ሎት 2. ጽዳት እቃዎች

በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች

1. በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፍቃድ
2. የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት
3. የቫት ተመዝጋቢነት የምስክር ወረቀት
4. የዘመኑ ግብር የተከፈለበት የምስክር ወረቀት ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዶች ጋር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ጨረታው በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በመልካ ጀብዱ ጤና ጣቢያ የግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቀርበው በብር 200 መግዛት ይችላሉ፡፡
6. የጨረታው ሳጥን በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡00 ተዘግቶ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል ፡፡ ነገር ግን በ16ኛው ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች ለጨረታው ማስከበሪያ የባንክ የተረጋገጠ CPO ብር 3,000 (ሶስት ሺህ ብር) ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ተጫራቾች በተጫራቾች መመሪያ መሰረት የመጫረቻ ሰነዱን ስርዝ ድልዝ ሳይኖረው በትክክል መሙላትና መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡
9. ጤና ጣቢያው ግዥውን ለመፈጸም የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0251-116-00-00 ወይም 0913919736 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡**

## ለሶስተኛ ጊዜ የወጣ የተሽከርካሪና የሞተር ሳይክል ጥገና ጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ግዢ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ለ2016 በጀት ዓመት ከዚህ በታች በሎት /LOT/ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት በዘርፉ የተሰማሩ አቅራቢዎች እንዲሣተፉ ይጋብዛል፡፡

- ሎት /LOT/ 1/አንድ፡- የመኪና ጥገና

1 በዘርፉ የታደሰየንግድ ፈቃድ ያላቸው

2 የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር /TIN NO/ / ያላቸው

3 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ

4 በዘርፉ የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው

5 የታተመ ቁጥር ያለው ደረሰኝ

6 የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10,000.00 አስር ሺ.ብር በባንክ የተረጋገጠ CPO ወይም በጥሬ ገንዘብማስያዝ የሚችሉ

- ሎት /LOT/ 2 የቢሮ የሞተር ሳይክል ጥገና

1 በዘርፉ የታደሰየንግድ ፈቃድ ያላቸው

2 የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር /TIN NO /ያላቸው

3 የታተመ ቁጥር ያለው ደረሰኝ

4 በዘርፉ የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው

5 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ

የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10,000.00 አስር ሺ. ብር በባንክ የተረጋገጠ CPO ወይም በጥሬ ገንዘብማስያዝ የሚችሉ

ከላይ የተጠቀሰውን መስፈርት የምታሟሉ ተጫራቾች

ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 5 ቀናት ዘወትር በሥራ ሰዓት በድሬዳዋ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ግዢ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ 3ተኛ ፎቅ በመቅረብ የጨረታውን ዝርዝር የያዘ ሰነድ የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመግዛት የሚጫረቱበትን ዋጋ ሞልተው በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለጨረታው በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ በማስገባት መወዳደር ይችላሉ፡፡

- ጨረታው በ 6ኛው ቀን ከጠዋቱ በ 3፡00 ሰዓት ታሽጎ በዛው እለት ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመሬት ልማትናማኔጅመንት ቢሮ ግዢ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 303 3ተኛ ፎቅይከፈታል፡፡ ሆኖም የጨረታ መክፈቻው ቀንበበዓል ቀናት ከዋለ በሚቀጥለው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል፡፡
- መ/ቤቱ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊልየመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 09-20-42-33-92--- 09-13-85-92-94 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡**

# የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ከድሬዳዋ አስተዳደር ዘመናዊ የሬድዮ መገናኛ ድጋፍ ተበረከተለት

- የሬድዮ መገናኛድጋፋ ለወንጀል መከላከልና ለትራፊክስራ አጋዥ ይሆናል

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ክቡር ኮሚሽነርዓለሙ መግራበድጋፍ ርክክቡ ወቅት እንደተናገሩት ይህ ዘመናዊ የሆነ የሬድዮ መገናኛ አሁን ላይ ተቋሙ የጀመረውን በቴክኖሎጂ የታገዘ የወንጀል መከላከል እና የትራፊክ ስራዎች ለማሳለጥ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡አንድ እርምጃ ቀዳሚ የሆነ የፖሊስ ተቋም ለመገንባት ለሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና እንደሚኖረውም ገልፀዋል፡፡



የድሬዳዋአስተዳደርም ሆነ ህዝቡ ከጎናችን ቆሞ ባለውለታችን ሲሆን መሰል ድጋፎች እኛን ባለዕዳ ነው የሚደርጉንያሉት ኮሚሽነር ዓለሙ መግራበዚህ ረገድ የእኛ ምላሽ ሊሆን የሚገባው በጀግነንት መጠበቅ በሰብአዊነት ማገልገልመርሀችንን ይዘን የከተማችንን ሰላም እና ደህንነት ማረጋገጥመሆኑን ጨምረው ገልፀዋል።

አስተዳደሩ ለድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ያደረገው ድጋፍ በዋጋ ሲተመን ከአንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር በላይየሚያወጣ ብዛቱ ሃምሳ የሆነ የሬድዮ መገናኛ ድጋፍ ማድረጉ ታውቋል።

# "ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት የጀርባ አጥንት የሆኑ አሽከርካሪዎችን ማክበር በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ብቻ ሳይሆን ሃላፊነታችን እና ግዴታችንም ጭምር ነው"

## የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሃር

የአዳማ ከባድ መኪና ሹፌሮች መረዳጃ ዕድር ማህበር የድሬዳዋ አስተዳደር ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለከባድ መኪና አሽከርካሪዎች ለሰጠው ክብር እና ዕውቅና የምስጋና መርሀ ግብር የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ክቡር አቶ ከድር ጁሃር እና የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ዋና አዛዥ ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ በተገኙበት ተካሂዷል ፡፡

በዝግጅቱ ላይ መልዕክት ያስተላለፉት የድሬዳዋ አስተዳደር ክቡር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር እንደገለፁት ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት የጀርባ አጥንት የሆኑ አሽከርካሪዎችን ማክበር በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ብቻ ሳይሆን ሃላፊነታችን እና ግዴታችንም ጭምር ነው ብለዋል።

ክቡር ከንቲባው አክለውም በተለይ ለሀገራችን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የአንበሳውን ድርሻ እየተወጡ ያሉ የከባድ መኪና ሹፌሮችእያበረከቱት ያለውን አስተዋጽኦ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ገልፀው፤ የአዳማ ከባድ መኪና ሹፌሮች መረዳጃ ዕድር ለአስተዳደሩ ለሰጡት ዕውቅና እና ክብር ላቅ ያለ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።



የድሬዳዋ ትራፊክ ፖሊስ ረጅም መንገድ በረሃ እና አስቸጋሪ የአየር ንብረት በመቋቋም የሀገራችን ገቢ እና ወጪ ንግድ ለሚያፋጥኑ የከባድ መኪና አሽከርካሪዎች የሚሰጠው ክብር ትልቅ ነው ያሉት የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ዋና አዛዥ ክቡር ኮሚሽነር ዓለሙ መግራ የከባድ መኪና አሽከርካሪዎች ወደ ከተማ ሲገቡ እና ሲወጡ መንገድ ከተሳሳቱ በፍቅር በማሳየት የማሻገር ተግባር ካልሆነ በስተቀርእነሱን የሚያማርር ተግባር እንደማይፈፀም ተናግረዋል ፡፡

የአዳማ ከባድ መኪና ሹፌሮች መረዳጃ ዕድር የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሚካኤል ፀጋዬ በበኩላቸው የድሬዳዋ አስተዳደር ለከባድ መኪና ሹፌሮች ላሳየው ክብር እና ፍቅር ማህበሩን በመወከል ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ከምስጋና መርሀ ግብሩመጠናቀቅ በኋላ የአስተዳደሩ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር እና ኮሚሽነር አለሙ መግራ በጋራ በመሆን ለከባድ መኪና አሽከርካሪዎች መልካም መንገድ በመመኘት ውሃ የማደል ተግባር አካሂደዋል ፡፡

# የበጎ ፍቃድ ስራዎች ካላቸው ማህበራዊ ፋይዳ ባሻገር ወጣቶችን ከፖሊስ ጋር እንዳቀራረቡ ተገለፀ

የክረምት በጎ ፈቃድ ስራዎች ላይ ተሳታፊ ለነበሩ አካላት በአዲስ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ አስተባባሪነት የምስጋና እና የእውቅናየማጠቃለያመድረክ ተካሄደ። የተከናወኑ በጎ ፍቃድ ስራዎች ካላቸው ማህበራዊ ፋይዳ ባሻገር የአካባቢውን ወጣቶች ከፖሊስ ጋር በሚገባ ያቀራረቡእንደነበርበመድረኩ ተገልጿል ፡፡

በምስጋና እና የእውቅና መድረኩ ላይ ተገኝተው መልዕክታቸውን ያስተላለፉት የወረዳው የህዝብ ተወካይ እና በድሬዳዋ አስተዳደር የስራ እና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ ክቡርአቶ ሮቤል ጌታቸው እንደተናገሩት በወረዳ 5 በክረምት ወራት የተከናወኑት የበጎ ፈቃድ ስራዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ የተሻለ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ሊበረታቱ የሚገባ እና ወጣቱ በበጎ ፈቃድ ስራዎች ላይ ያሳየው መነሳሳት በርካታ ስራዎችን ማከናወን እንደሚችል ማሳያመሆኑን ተናግረዋል።

በአሁን ሰዓት ወጣቶች በአካባቢያቸው ባሉ የስራ መስኮች ላይ ስራ ሳይመርጡ በመሰማራት ስራ አጥነት እና ወንጀልን በጋራ መከላከል እንደሚገባ ጠቅሰው በቀጣይ አስራ አምስት የሚሆኑ የአካባቢው ወጣቶችን



በተለያዩ የሞያ መስኮች ለማሰልጠን ቃል ገብተዋል ፡፡

በመድረኩ ላይ ተገኝተው መልዕክታቸውን ያስተላለፉትየአዲስ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ዋ/ኢ/ር ብስራት ጫኔ በበኩላቸው እንደተናገሩት በ2015 ዓ.ም በተከናወኑ የበጎ ፈቃድ ስራዎች በቀጣይ በበጋ ወራትም ለማስቀጠል አቅም የተፈጠረበት እና ከማህበራዊ ፋይዳው ባሻገርበፖሊስ እና በአካባቢው ወጣቶችመካከል መልካም ግንኙነት እና መቀራረብን የፈጠረ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል።

የአካባቢው ወጣቶች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በሚፈጠሩ የትኛውም አይነት ጉዳዮች ከጣቢያው ጋር ተቀራርቦ በመስራት ላይ እንደሚገኙ እና ከዚህ በፊት በተደረጉ ውይይቶች በአካባቢው ላይ ከትራንስፖርት ጋርይስተዋሉ የነበሩ ችግሮችን ለመቅረፍ ውይይቶችን በማካሄድ መፍትሄ ከማስቀመጥ ባሻገር ቁጥራቸው30 ለሚሆኑ የአካባቢው ወጣቶች ጣቢያው ባመቻቸውእድል የመንጃ ፈቃድ የማውጣት ስራዎች ማከናወናቸውን እና በቀጣይ ወጣቶችን በተለያዩ ማህበራት ለማደራጀት የተለያዩ አካላትን በማነጋገር ወደ ስራመግባታቸውን ጨምረው ተናግረዋል ፡፡

በመድረኩ ላይ በክረምት የበጎ ስራዎች ላይ ተሳትፎ ላደረጉ አካላት እንደ አስተዋፅኦ ደረጃቸው የእውቅና ምስክር ወረቀት እና ዋንጫ የተበረከተላቸው ሲሆን በመድረኩ ላይም የወረዳ 5 አስተዳደር አመራሮች እና የጣቢያው አመራር እና አባላት እንዲሁም የክረምት በጎ ፈቃድ ስራዎች ላይ የተሳተፉና ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰቦች ተገኝተዋል፡፡

# የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ ከአማካሪ ምክር ቤት እና በቀጠናው ከሚገኙ ማህበረሰብ ጋር የአንደኛ ሩብ አመት የስራ ግምገማ መድረክ አካሄደ



የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያአዛዥ ዋ/ኢ/ር ሻምበል ተካልኝ በመድረኩ ላይ እንደተናገሩት በ 2016 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ አመት የተከናወኑ ስራዎች ነፃ በሆነ ሀሳብ ለመጀመሪያ ግዜ በህዝብ የማስገምገም መድረክ መዘጋጀቱ ድክመቶችን በማረም ጠንካራ ጎኖችን ለማስቀጠል ጥቅሙ የጎላ መሆኑን ጠቅሰው፤ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ እያከናወነ የሚገኘውን የለውጥ ግስጋሴ ለማስቀጠል የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ የዜጎችን ሰብአዊ መብት በማክበር በቀጠናው አስተማማኝ ሰላም ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ ተናግረዋል ፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ የተገኙት የቀበሌ 01 ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሳላህ መሀመድ እንደተናገሩትካለፉትሶስት እና አራት አመት በፊት ማህበረሰቡ እና ፖሊስ ተራርቀው የአካባቢው ሰላም ታውኮ እንደነበር አስታውሰው አሁን ላይ ማህበረሰቡ ከፖሊስ ጋር ያለው ጤናማ ግንኙነት የላቀ በመሆኑ የአካባቢው ሰላምሊረጋገጥ መቻሉን ተናግረዋል፡ ፡ የመልካ ጀብዱ ፖሊስ ጣቢያ ባልተለመደ ሁኔታ ግልጽ በሆነ መንገድ ስራዎችን በህብረተሰቡ ማስገምገም መቻሉ ለቀጣይ ጠንካራ ስራን ለመስራት የሚረዳ እና ለሌሎች ፖሊስ ጣቢያዎችም ተሞክሮ ሊሆን እንደሚገባ አስታውቀዋል ፡፡

በዚህም የግምገማ መድረክ ከቤቱ ሰፊ ሀሳቦች የተሰነዘሩ ሲሆን የጣቢያው ሀላፊ ዋ/ኢ/ርሻምበል ተካኝ እና የቀበሌው ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሳላህ መሀመድ ምላሽ እና ማብራሪያ በመስጠት የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ መድረኩ ተጠናቋል ፡፡

# ህጉ ምን ይላል?

## ስለ መቃወሚያ

በፍትሐብሔር 358 መሰረት መቃወሚያ ለማቅረብ ስለሚችሉ ወገኖች በሚለው ስር እንዲህ የሚል ተገልጾ እናገኛለን፡፡ “በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው (በክርክሩ) ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው ራሱ (ጠበቃው) (ነገረ ፈጁ) ተካፋይ ባልሆነበትና ክርክር የተሰጠው ፍርድ ከመፈፀሙ በፊት መቃወሚያውን ለማቅረብ ይቻላል፡፡

ይህ ጉዳይ ፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔ እንደገና እንዲያየው ከሚያደርግባቸው ምክንያቶች አንዱ በተሰጠው ውሳኔ ምክንያት በ3ኛ ሰው ላይ ጉዳት መድረሱ ማመልከቻ በቀረበ ጊዜ ነው፡፡ ይኸውም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት በክርክር ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው(በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችል) እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ ፍርድ ከመፈፀሙ በፊት ለፍርድ ቤት መቃወሚያውን ማቅረብ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ ማመልከቻው የሚቀርበው በክስ ማመልከቻ በሚቀርብበት ፎርም ይሆናል የቀረበው አቤቱታ ከአፈፃፀም በኋላ ከሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህ ጉዳይ ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 40 አንፃርም መታየት ያለበት ሲሆን በዚህ ቁጥር መሰረት ተከራካሪ ወገኞች በክርክሩውስጥ ባለመጨመራቸው ወይም ባለመተካታቸው ምክንያት የተፈጠረው ችግር ከተደነገገው አንፃር ሊታይ ይገባል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 418 መሰረት ደግሞ በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለኝ ባዮች በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር ወይም በዚሁ ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ በማለት ተቃወሞ የማቅረብ መብት ያላቸዉ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡




19ኛ ዓመት | ቁጥር 851 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ - ጥቅምት / 28 / 2016 ዓ.ም

# የድሬዳዋ ስታዲየም እደሳ እየተጠናቀቀ ይገኛል

በብሩክ ደስታ

በሊጉ የሚደረጉ የ2ኛውን ዙር ጨዋታዎች ለማስተናገድ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ የድሬዳዋ አስተዳደርክቡር ከንቲባአቶ ከድር ጁሃር ገልፀዋል።

ይህ በርካታ አህጉር አቀፍ ውድድሮችን እንዲሁም ሀገር አቀፍ ሁነቶችን ሲያስተናግድ የኖረው አንጋፋው የድሬዳዋስታዲየም ማስፋፊያ ግንባታ አሁን ዘመኑንከሚመጥንበት ደረጃደርሷል።

በዚህ ወቅት የከተማዋን ስም የሚመጥን ኢንተርናሽናል ስታዲየም ዘመናዊና ደረጃውን የጠበቀ የእግር ኳስ መጫወቻአርቴፊሻል ሳር ሜዳ ስራው እየተፋጠነ ይገኛል፡፡ የሜዳውን ሣር እድሳት በባለቤትነት የሚመራው የድሬዳዋ ወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን የመጫወቻ ሜዳውን ሣር የማንጠፍ ስራ አስመልክቶ፣ የሚዲያ አካላት ፕሮጀክቱን እንዲጎበኙትአድርጓል፡፡





የስታዲየሙን ሣር እድሳት የተመለከቱት የድሬዳዋ አስተዳደርክቡር ከንቲባ አቶ ከድርጁሃርእንደተናገሩት "ድሬዳዋንበስፖርቱ ተወዳዳሪና ተመራጭ ከተማ ለማድረግ ኢንተርናሽናልውድድሮችን የማስተናገድ አቅሟን ለማሳደግአስተዳደሩ ዘመናዊ የስፖርት መሠረተ ልማቶችን እያስፋፋ ነው ብለዋል፡፡ "የስታዲየሙ ሣር አለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ በጥንቃቄ እየተሰራ እንዳለ የጠቆሙት ከንቲባው የፊፋ እውቅናን እንደሚያገኝም ገልፀዋል"፡፡ በአስተዳደሩ ከፍተኛ ወጪ ሜዳውን በሰው ሰራሽ ሣር የመቀየር ስራ ተጠናቆ የፕሪሚየር ሊጉን ጨዋታዎች እንደሚያስተናግድም ነው የተገለፀው ፡፡"

የድሬዳዋ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት ኮሚሽነር አለሙ መገራ በበኩላቸው " የከተማዋን ስፖርት ለማሳደግ አስተዳደሩ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ የገለፁ ሲሆን ባለፉት ጊዜያቶች በእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው እንደሚሰሩምነው የተናገሩት፡፡

"የስታዲየሙን ሰው ሰራሽ ሣር ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ በአስተዳደሩ መሸፈኑን የወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ፊራኦል ቡልቻ አስታውቀዋል፡፡ መጫወቻ ሣሩ በተለይ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን በማሰብ ከውጪ በመጡ ባለሙያተኞች ጭምርመሰራቱን የቢ.ቲ .ኤ .ኤን TANኢንጅነሪንግ ትሬዲንግ ማንጀር አቶ ፉሀድ ኢብራሂም ገልፀዋል፡፡

አሁን ላይ በኢትዮጵያ የተገነቡስታዲየም የዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኅበር (ፊፋ) ለዚህ ወቅት የሚመጥን አይደለም በሚል ማንኛውንም አኅጉራዊም ይሁን ዓለም አቀፋዊ ውድድሮችን እንዳያስተናግዱ ክልከላ ጥሎበታል፡፡ ይህንን የተረዳው የድሬዳዋ አስተዳደር በተለያዩ ምዕራፍ የማሻሻያ ሥራና ዕድሳት እየተደረገለት የሚገኘው የድሬዳዋ ስታዲየም አለማአቀፍ ደረጃውን የሚያሟላ የመጫወቻው ሜዳ አሁን ላይተስፋ ሰጪ መሆኑ እየተነገረለት ይገኛል፡ ፡ የመጫወቻ ሜዳው ብቻውን 68 በ10 5 ሜትር የሚሸፍን መሆኑም ተነግሯል፡፡

**ምንጭ:- የድሬዳዋ ወጣቶችና ስፖርት ኮምሽን**

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አዳዲስ አሰልጣኞችን አግኝቷል




ያለፉትን ወራት በጊዜያዊ አሠልጣኝ ሲመራ የነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌን በቋሚነት ማግኘቱ ይታወቃል። አሠልጣኙ አመሻሽ ላይ ለ30 ተጫዋቾች ጥሪ በማቅረብ ከፊታቸው ላለባቸው የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ ዝግጅታቸውን ከመጀመራቸው አንድ ቀን አስቀድሞ ደግሞ ረዳቶቻቸውን ለይተዋል።

በዚህም አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ የብሔራዊ ቡድኑ ረዳት አሠልጣኝ በመሆን መመረጣቸው ታውቋል። የቀድሞ የወላይታ ዲቻ፣ ፋሲል ከነማ እና አርባምንጭ ከተማ አሠልጣኝ የነበሩት መሳይ ዓምና የሊጉ የመገባደጃ ሳምንታት ላይ ከአዞዎቹ ጋር ከተለያዩ በኋላ ያለ ኃላፊነት ተቀምጠው የነበረ ሲሆን አሁን የዋልያዎቹ ረዳት በመሆን የአንድ ዓመት ውል ፈርመዋል።

የግብ ጠባቂዎች አሠልጣኝ በመሆን ደግሞ በአሠልጣኝ ውበቱ አባተ ዘመን የግብ ዘቦች አሠልጣኝ የነበረው አሠልጣኝ ደሳለኝ ገብረጊዮርጊስ ዳግም ወደ ብሔራዊ ቡድኑ ተመልሷል።

አሰልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ዋና አሰልጣን በመሆን በአንድ ዓመት ውል መሾማቸው ይታወሳል።

# አራት ተጫዋቾች ብሔራዊ ቡድኑን አልተቀላቀሉም



ለዓለም ዋንጫ ማጣርያ ዝግጅታቸውን የጀመሩት ዋልያዎቹ በዝግጅታቸው አራት ተጫዋቾች አልተገኙም።

አሰልጣኝ ገብረመድኅን ኃይሌን በዋና አሰልጣኝነት የሾመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በቀጣይ ኅዳር ወር መጀመርያ ላይ ከሴራልዮን እና ቡርኪናፋሶ ጋር በሞሮኮ ሀገር ለሚያደርገው የዓለም ዋንጫ ማጣርያ ጨዋታዎች በቅርቡ ለ30 ተጫዋቾች ጥሪ በማድረግ ባሳለፍነው ሳምንት በአዳማ አበበ ቢቂላ ስታዲየም የመጀመርያ ዝግጅቱን ጀምሯል።

26 ተጫዋቾች በመጀመሪያ ቀን ልምምድ የተገኙ ሲሆን አራት ተጫዋቾች በዝግጅቱ ላይ እንዳልተሳተፉ አረጋግጠናል። እነርሱም ጌታነህ ከበደ፣ ሽመልስ በቀለ፣ ጋቶች ፓኖም እና ጉዳት ላይ የቆየው አቡበከር ናስር መሆናቸውን ተረጋግጧል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አጥቂው ጌታነህ ከበደ ከብሔራዊ ቡድን ስብስብ ውጭ መሆኑ እየተሰማ ነው።

ጌታነህ ብሔራዊ ቡድኑ ባረፈበት ካኖፒ ሆቴል በአካል በመገኘት ከዋልያዎቹ አለቃ ገብረመድህን ኃይሌ ጋር ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ አስቀድሞ ራሱን ከብሔራዊ ቡድኑ በማግለሉ ለጨዋታው ዝግጁ አለመሆኑን ተከትሎ ከቡድኑ ጋር አብሮ እንደማይቀጥል አሳውቋል ተብሏል።

**ምንጭ፡- ሶከር ኢትዮጵያ**